lawyer.et

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ሰባተኛ ዓመት ቁጥር ፳፮
አዲስ አበባ ሚያዚያ ፲፰ ቀን ፳፻፲፫ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

27th Year No.26
ADDIS ABABA 26th April, 2021

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፴፬/፳፻፲፫

የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ……..ገጽ ፲፫ሺ፪፻፳፮

## Content

Proclamation No.1234/2021

Federal Courts Proclamation…..............Page 13226

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፴፬/፳፻፲፫
## የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ህገ-መንግስት የዳኝነት ሥልጣን በፌደራል እና በክልሎች ፍርድ ቤቶች በመሆኑ፤

ማንኛውም ሰው በፍርድ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ለፍርድ ቤት የማቅረብና ዉሳኔ ወይም ፍርድ የማግኘት መብት ያለዉ መሆኑ፤በህገ መንግስቱ የተደነገገ በመሆኑ፤

የፌደራል ፍርድ ቤቶች ለሕግ የበላይነት፣ ለሰብዓዊ እና ዲሞክራሲያዊ መብቶች መከበር የበኩላቸውን የማይተካ ሚና የሚወጡበትን ሥርዓት መዘርጋት በማስፈለጉ፤

የፌደራል ፍርድ ቤቶች በሕገ መንግሥቱ ስለዳኝነት ነፃነት በተደነገገዉ መሠረት ተግባራቸውን ተጠያቂነት ባለበት ሁኔታ ውጤታማ ፣ ቀልጣፋ ፣ ተደራሽ እና ተገማች የሆነ አገልግሎት መስጠታቸው አስፈላጊ በመሆኑ፤

የዳኝነት ሥርዓቱን ለማጠናከር የፌደራል ፍርድ ቤቶች በበጀት ምደባና አስተዳደር፣በሰው ሀብት ቅጥርና ምደባ እንዲሁም አስተዳደር ራሳቸውን ችለው የሚሰሩበትን የሕግ ማዕቀፍ እና የአሰራር ሥርዓት መዘርጋት አስፈላጊ በመሆኑ፤

## PROCLAMATION NO.1234/2021
## FEDERAL COURTS PROCLAMATION

WHEREAS, in the Federal Democratic Republic of Ethiopia Constitution, judicial power is vested in both the Federal and the Regional courts;

WHEREAS, the Constitution stipulates that everyone has a right to bring justiciable matter to obtain a decision or judgment from, a court of law; irreplaceable;

WHEREAS, it is necessary to establish a system in which Federal Courts play an inimitable role in enforcing the rules of law and, protection of human and democratic rights;

WHEREAS, it is necessary to ensure that Federal Courts do provide effective, efficient, accountable and predictable service in accordance with judicial independence mentioned in the provision of the Constitution;

WHEREAS, establishing a legislative framework under which courts would have full autonomy to manage their own budget, recruit and assign their non-judicial personnel, and administer themselves is essential for a strong judiciary;

lawyer.et



የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፰ በተደጋጋሚ መሻሻሉ ለአሰራር አመቺ ባለመሆኑና በተሻሻለ አዋጅ መተካት ስላስፈለገ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀፅ (፩) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

## ምዕራፍ አንድ
## ጠቅላላ

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፴፬/፪ሺ፲፫" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### ፪. ትርጓሜ

በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

፩/ "ሕገ መንግስት" ማለት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት ነው፤

፪/ "የፌደራል መንግሥት ሕጎች" ማለት በፌደራል መንግሥቱ ሥልጣን ክልል ሥር የሚወድቁ ጉዳዮችን የሚመለከቱ፡ በሥራ ላይ ያሉ ሕጎችን ይጨምራል፤

፫/ "ፌደራል ፍርድ ቤቶች" ማለት የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ናቸው፤

፬/ "መሠረታዊ የሆነ የህግ ስህተት" ማለት ቀጥሎ ከተዘረዘሩት መካከል አንዱ እና ፍትህን የሚያዛባ ጉልህ የህግ ስህተት ያለበትን በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲ መሰረት በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት ሊታዩ የሚችሉ የመጨረሻ ዉሳኔ፣ ፍርድ፣ ብይን፣ትእዛዝ፣ ናቸው ፡-

ሀ) የሕገ መንግሥቱን ድንጋጌዎች የሚቃረን፤

ለ) ሕግን አላግባብ የሚተረጉም ወይም ለጉዳዩ አግባብነት የሌለውን ሕግ የሚጠቅስ፤

ሐ) ለክርክሩ አግባብነት ያለው ጭብጥ ሳይያዝ ወይም ከክርክሩ ጋር የማይዛመድ አግባብነት የሌለው ጭብጥ ተይዞ የተወሰነ፤

WHEREAS, the frequent amendment of the Federal Courts Proclamation No. 25/1996 makes inconvenience to work and necessary of having an amended Proclamation;

NOW THEREFORE, in accordance to the Article 55 Sub-Article (1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

## CHAPTER ONE
## GENERAL

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Federal Courts Proclamation No. 1234/2021"

### 2. Definitions

In this proclamation:

1/ "Constitution" means the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia;

2/ "Laws of the Federal Government" includes all laws in force that are consistent with the Constitution and relating to matters that fall within the competence of the federal government as specified in the Constitution;

3/ "Federal Courts" means the Federal Supreme Court, the Federal High Court and the Federal First Instance Court;

4/ "Basic or fundamental error of law" shall be final judgment, ruling, order or decree which may be filed in Federal Supreme Court Cassation division pursuant to Article 10 of this Proclamation and/or contains either one or similar of the following basic errors and grossly distresses justice:

a) in violation of the constitution

b) by misinterpreting a legal provision or by applying an irrelevant law to the case;

c) by not framing the appropriate issue or by framing an issue irrelevant to the litigation;

lawyer.et



መ) በዳኝነት ታይቶ ሊወሰን የሚገባውን ጉዳይ ውድቅ በማድረግ የተወሰነ፣

ሠ) በፍርድ አፈጻጸም ሂደት ከዋናው ፍርድ ጋር የማይገናኝ ትእዛዝ የተሰጠበት፣

ረ) ጉዳዩን አይቶ የመወሰን የዳኝነት ሥልጣን ሳይኖር የተወሰነ ፣

ሰ) የአስተዳደር አካል ወይም ተቋም ከህግ ዉጭ የሰጠው ውሳኔ፣

ሸ) የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትን አስገዳጅ ውሳኔ በመቃረን የተወሰነ፡፡

፭/ "የመጨረሻ ውሳኔ" ማለት በፍርድ ቤት ፣ በሕግ የመዳኘት ሥልጣን በተሰጠው አካል፣ በተቋማት ወይም በአማራጭ የክርክር መፍቻ ዘዴዎች የተሰጠ እና ለጉዳዩ እልባት የሚሰጥ ፍርድ ፣ ብይን፣ ትዕዛዝ፣ ውሳኔ እና/ወይም የይግባኝ ሂደቶችን የጨረሰ ፍርድ፣ ብይን፣ ትዕዛዝ ወይም ውሳኔን ይጨምራል፣

፮/ «የፌደራል መንግስት ባለስልጣኖች» ማለት የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት እና የፌዴሬሽን ምክር ቤት አባላት፣ ከሚኒስቴር ደረጃ በላይ የሆኑ የፌደራል መንግስቱ ባለስልጣኖች፣ ሚኒስትሮች እና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች እና በተመሳሳይ ደረጃ ላይ የሚገኙ የፌደራል መንግስት ባለስልጣኖች ናቸዉ፣

፯/ «የፌደራል መንግስት ሰራተኞች» ማለት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፯ ስር ከተጠቀሱት ዉጭ ያሉ በፌደራል መንግስት ስራ ላይ የተሰማሩ ሰራተኞች ሁሉ ያጠቃልላል፣

፰/ "የአስተዳደር ሠራተኛ" ማለት ከዳኛ እና ከተሿሚ የአስተዳደር ሰራተኛ ዉጭ ያለ ሁሉንም የፍርድ ቤት ሰራተኛ ያጠቃልላል፣

፱/ "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠዉ ሰዉ ነዉ፣

፲/ "የከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች" ማለት በአዲስ አበባ ከተማ አሰተዳደር ቻርተር አዋጅ መሠረት የተቋቋመ የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤት እና በድሬዳዋ ከተማ አስተዳደር ማቋቋሚያ ቻርተር አዋጅ መሠረት የተቋቋመ ፍርድ ቤት ማለት ነው፣

፲፩/ በዚህ አዋጅ በወንድ ፆታ የተደነገገው የሴትንም ፆታ ያካትታል፡፡

d) by denying to an award judgment to a justiciable matter;

e) by giving an order in execution proceedings unwarranted by the main decision;

f) in the absence of jurisdiction over the subject matter in dispute;

g) an administrative act or decision rendered in contradiction with the law;

h) in contravention to binding decision of the Federal Supreme Court Cassation Division.

5/ "Final decision" shall include judgment, ruling, order or decree that finally disposes the case and/or decision, ruling, order or judgement that has completed the possible appeal mechanisms and rendered by courts, organ vested with judicial power, by institutions or an alternative dispute resolution mechanism;

6/ "Officials of the Federal Government" means members of the House of Peoples' Representatives and of the House of the Federation, officials of the Federal Government above Ministerial rank, Ministers, Judges of the Federal Supreme Court and other officials of the Federal Government of equivalent rank;

7/ "Employees of the Federal Government" includes all employees, other than those referred to under Sub-Article (1) hereof, engaged in the activities of the Federal Government;

8/ "Administrative workers mean non-judicial court employees excluding judges and assignees;

9/ "Person" means a natural or juridical person;

10/ City Court mean the Addis Ababa City Court and DireDawa City Court which have been established pursuant to the respective Charters of City Administration;

11/ in this Proclamation Any expression in the masculine gender includes the feminine.

lawyer.et



## ምዕራፍ ሁለት

## ስለ ፌደራል ፍርድ ቤቶች የወል የዳኝነት ሥልጣን

### ፫. መሠረቱ

፩/ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሚከተሉት ላይ የዳኝነት ሥልጣን ይኖራቸዋል፦

ሀ) ሕገ መንግሥቱን፣ የፌደራል መንግሥቱን ሕጎች ወይም ኢትዮጵያ የተቀበለቻቸዉ እና ያፀደቀቻቸዉ ዓለም አቀፍ ስምምነቶችን መሠረት በማድረግ በሚነሱ ጉዳዮች፣

ለ) በፌደራል መንግሥቱ ሕግ ተገልጸው በተወሰኑ ባለጉዳዮች፤

ሐ) በሕገ መንግሥቱ ወይም በፌደራል መንግስት ሕግ በተገለጹ ቦታዎች፡፡

፪/ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች በሚሰጡት የዳኝነት አገልግሎት በህገ መንግስቱ አንቀጽ ፱(፪) እና ፲፫(፩) መሰረት የህገ መንግስቱን ድንጋጌወች ተግባራዊ ያደርጋሉ።

### ፬. የወንጀል የዳኝነት ሥልጣን

የፌዴራል ፍርድ ቤቶች በሚከተሉት የወንጀል ጉዳዮች ላይ የዳኝነት ሥልጣን ይኖራቸዋል፦

፩/ በአገር ላይ በሚፈፀሙ ወንጀሎች፣

፪/ በውጭ ሀገር መንግሥት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች፣

፫/ ዓለም አቀፍ ሕጐችን በመጣስ የሚፈፀሙ ወንጀሎች፤

፬/ ከአንድ ክልል በላይ ወይም በዓለም አቀፍ ደረጃ አገልግሎት በሚሰጡ መገናኛዎች ደህንነትና ነፃነት ላይ የሚፈጸሙ ወንጀሎች፣

፭/ የበረራ ደህንነትን የሚመለከቱ ወንጀሎች፤

፮/ ዓለም አቀፍ የዲፕሎማቲክ ሕጎችና ልምዶች እንዲሁም ኢትዮጵያ አባል የሆነችባቸው ሌሎች ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እንደተጠበቁ ሆነው፤ የውጭ ሀገር አምባሳደሮች፣ ቆንስሎች፣ የዓለምአቀፍ ድርጅቶች፣ የውጭ መንግሥታት ወኪሎች ተጠያቂ በሚሆኑባቸው ወይም ልዩ መብትና ጥበቃ ያላቸው በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩ የውጭ ሀገር ሰዎች ተበዳይ ወይም ተከሳሽ የሆኑባቸው ወንጀሎች፣

፯/ የአደገኛና አደንዛዥ ዕጾች ሕገ-ወጥ ዝውውርን የሚመለከቱ ወንጀሎች፣

## CHAPTER TWO

## COMMON JURISDICTION OF FEDERAL COURTS

### 3. Principle

1/ Federal Courts shall have jurisdiction over the following:

a) Cases arising under the Constitution, Federal Laws and International Treaties accepted and ratified by Ethiopia;

b) Parties specified in Federal Law,

c) Places specified in the Constitution or by Federal Law.

2/ Federal courts shall interpret and observe the provisions of the Constitution pursuant to Article 9(2) and 13(1) of the Constitution.

### 4. Criminal Jurisdiction

Federal Courts shall have jurisdiction over the following criminal cases:

1/ crimes against the national state;

2/ crimes against foreign state;

3/ crimes in violation of international laws;

4/ crimes regarding the security and freedom of communication services operating in more than one Region or at International level;

5/ crimes against the safety of aviation;

6/ Without prejudice to international diplomatic laws and customs as well other international agreements to which Ethiopia is a party, crimes of which foreign ambassadors, consuls, representatives of international organizations, foreign states are held liable or foreign nationals who enjoy privileges and immunities and who reside in Ethiopia are victims or defendants;

7/ crimes regarding illicit trafficking of dangerous drugs;

lawyer.et


፰/ በተለያዩ ክልሎች ወይም በፌደራልና በክልል ፍርድ ቤቶች የሥልጣን ክልል ሥር በሚወድቁና በተያያዙ ወንጀሎች፣

፱/ በተለያዩ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች፣ ጎሣዎች፣ በሀይማኖት ተከታዮች ወይም በፖለቲካ ቡድኖች መካከል ከተፈጠረ ግጭት ጋር የተያያዙ ወንጀሎች፣

፲/ በፌደራል መንግሥት የቀረጥና የግብር ገቢዎች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች፤

፲፩/ በፌደራል መንግሥት የገንዘብ እና ኢኮኖሚ ጥቅሞች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች፤

፲፪/ በታወቁ ገንዘቦች፣የግዴታ ወይም የዋስትና ሰነዶች፣ ቴምብሮች ወይም መሳሪያዎች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎች፤

፲፫/ የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፪ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና አንቀጽ ፲፭ ንዑስ አንቀጽ (፪) እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ከ፭ ዓመት ጽኑ እሥራት በላይ ሊያስቀጡ የሚችሉ የውጭ ሀገር ዜጎች ተበዳይ ወይም ተከሳሽ የሆኑባቸው ወንጀሎች፣

፲፬/ የፌደራል መንግሥት ባለሥልጣኖች በማናቸዉም የወንጀል ጉዳዮች እና የፌደራል መንግስት ሠራተኞች በሥራቸው ወይም በኃላፊነታቸው ምክንያት ተጠያቂ የሚሆኑባቸው የወንጀል ጉዳዮች፤

፲፭/ በፌደራል መንግሥት ንብረቶች ላይ በሚፈጸሙ እና የአዋጁ አንቀጽ ፲፪ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና አንቀጽ ፲፭ ንዑስ አንቀጽ (፪) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከ፭ ዓመት ጽኑ እሥራት በላይ ሊያስቀጡ የሚችሉ ወንጀሎች፤

፲፮/ ለከተማ አሰተዳደር ፍርድ ቤቶች በቻርተር አዋጅ ከተሰጣቸው የደንብ መተላለፍ እና በወንጀል ሕግ ሥነ-ሥርዓት እና የማስረጃ ሕግ መሠረት የሚቀርቡ የብርበራ ትዕዛዝ፣ የመያዣ ትዕዛዝ፣ የእምነት ቃል፣ የተያዘ ሰው በተመለከተ በጊዜ ቀጠሮ ጥያቄና የዋስትና ጉዳይ ላይ መርምሮ ትዕዛዝ መስጠት ጉዳዮችን ከማየት በተጨማሪ በግል አቤቱታ አቅራቢነት የሚያስከስሱ የወንጀል ጉዳዮችን የሚመለከቱ ሆኖ ከእነዚህ ውጭ ያሉ የወንጀል ጉዳዮች በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሚዳኙ ይሆናሉ፤

፲፯/ በሌሎች ሕጎች በተጠቀሱ ጉዳዮች፡፡

8/ crimes falling under the jurisdiction of courts of different regions or under the jurisdiction of both the federal and regional courts as well as concurrent offences;

9/ crimes connected with conflicts between various nations; nationalities, ethnic, religious or political groups;

10/ crimes against customs duty and tax revenues of the Federal Government;

11/crimes against the fiscal and economic interests of the Federal Government;

12/ crimes against currencies, government bonds or security documents, official seals, stamps or instruments;

13/ without prejudice to Article 12 Sub-Article (2) and Article 15 Sub-Article (2), crimes of which foreigners are victims or defendants that entailing more than 5 years' rigorous imprisonment;

14/ crimes committed by officials and employees of the Federal Government in connection with their official responsibilities or duties;

15/ without prejudice to Article 12 Sub-Article (2) and Article 15 Sub-Article (2) of this Proclamation, crimes committed against the property of the Federal Government and which entail more than 5 years' rigorous imprisonment;

16/ City Administration courts in accordance to Charter Proclamation In addition to reviewing cases related to violations of rules and criminal procedure and procedure code based decisions of search, confession, arrest warrant, inquiry in to appeals and guarantees in appeal. other criminal cases will be heard in Federal Courts;

17/ Cases specified by other laws.

lawyer.et



## ፭. የፍትሐ ብሔር የዳኝነት ሥልጣን

፩/ የፌደራል ፍርድ ቤቶች በሚከተሉት የፍትሐ ብሔር ጉዳዮች ላይ የዳኝነት ሥልጣን ይኖራቸዋል፦

ሀ) የግለሰብ ዓለም አቀፍ ሕግን በሚመለከቱ ጉዳዮች፤

ለ) የውጭ ሀገርን ፍርድ ወይም ብይን ለማስፈፀም በሚቀርብ አቤቱታ፤

ሐ) ዜግነትን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ በሚነሱ ክርክሮች፣

መ) ከመክሰር ጋር በተያያዙ ጉዳዮች፤

ሠ) ዓለም አቀፍ የዲፕሎማቲክ ሕጎችና ልምዶች እንዲሁም ኢትዮጵያ አባል የሆነችባቸው ሌሎች ዓለም አቀፍ ስምምነቶች እንደተጠበቁ ሆነው፤ የውጭ ሀገር አምባሳደሮች፣ ቆንስላዎች፣ የዓለም አቀፍ ድርጅቶች፣ የውጭ መንግሥታት ወኪሎች ተጠያቂ በሆኑባቸው ወይም/እና ልዩ መብትና ጥበቃ ያላቸው በኢትዮጵያ ውስጥ የሚኖሩ የውጭ ሀገር ሰዎች ተከራካሪ በሆኑበት ጉዳዮች፣

ረ) የፌደራል መንግሥት አካል ተከራካሪ በሆነበት ጉዳይ

ሰ) የፌደራል መንግሥቱን ንብረቶች በተመለከተ የሚነሱ ጉዳዮች፤

ሸ) መደበኛ ነዋሪነታቸው በተለያዩ ክልሎች፣ በክልል እና በአዲስ አበባ ከተማ፣ በክልል እና በድሬዳዋ ከተማ፣ በአዲስ አበባ ወይም በድሬዳዋ ከተማ ውስጥ በሆኑ ሰዎች መካከል የሚነሱ ጉዳዮች፣

ቀ) የፌደራል መንግሥቱ ባለሥልጣኖችና ሠራተኞች በስራቸዉ ወይም በሃላፊነታቸዉ ምክንያት ኃላፊ በሚሆኑባቸው ጉዳዮች፣

በ) የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፩ ንዑስ አንቀጽ (፪) እና አንቀጽ ፲፭ ንዑስ አንቀጽ (፪) ላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ፤ የውጭ አገር ዜጋ ከሳሽ ወይም ተከሳሽ የሆነበት ጉዳይ፤

ተ) በፌደራል መንግሥቱ አካላት የተመዘገቡ ወይም የተቋቋሙ የንግድ ድርጅቶችና ማህበሮችን በሚመለከት የሚነሱ ክርክሮች፣

ቸ) የሚተላለፉ የገንዘብ ሰነዶች በተመለከተ የሚነሱ ክርክሮች ፤

## 5. Civil Jurisdiction

1/ Federal Courts shall have jurisdiction over the following civil cases:

a) Regarding private international law;

b) Application regarding the enforcement of foreign judgment or decision;

c) involving matters of nationality;

d) Issues in relation to bankruptcy;

e) Without Prejudice to international diplomatic laws and customs as well as other international agreements to which Ethiopia is a party, cases of which foreign ambassadors, consuls, representatives of international organizations, foreign states are held liable or foreign nationals who enjoys privileges and immunities and who resides in Ethiopia are parties;

f) Cases to which a federal government organ is a party;

g) cases involving the property of the federal government;

h) Cases arising between persons permanently residing in different regions, regions and Addis Ababa, regions and Diredawa, Addis Ababa or DireDawa;

i) cases of involving the liability of officials or employees of the federal government in connection with their official responsibilities or duties;

j) without prejudice to Article 12 Sub-Article (2) and Article 15 Sub-Article (2) of this Proclamation, cases in which foreigner is a plaintiff or a defendant;

k) cases involving business organizations and associations registered with, or established by, federal government organs;

l) cases involving negotiable instruments;

lawyer.et



አ) በፈጠራ፣ በድርሰትና ሥነ ጥበብ፣ ቅጅ እና ተዛማጅ መብቶች ባለቤትነት በተመለከተ የሚነሱ ክርክሮች፣

ነ) የኢንሹራንስ ውልን በተመለከተ የሚነሱ ክርክሮች፣

ኘ) ተገዶ የመያዝ ሕጋዊነትን ለማጣራት የሚቀርብ አቤቱታ፤

ደ) ለከተማ አስተዳደር ፍርድ ቤቶች በቻርተር አዋጅ የተሰጣቸው የፍትሀብሄር ዳኝነት ሥልጣን ማለትም በወሳኝ ኩነት ምዝገባ እና መታዎቂያ ወረቀት ህግ መሠረት በሚሰጥ ሰነድ ጋር በተያያዘ፣ ከስም ለውጥ፣ ከመጥፋት፣ የፍርድ ክልከላ፣ የባልነት ሚስትነት የአሳዳሪነት የሞግዚትነት ማስረጃ ይሰጠን ጉዳይ፣ የከተማው አስተዳደር ከሚያስተዳድረው ቤት ጋር በተያያዘ በሚነሳ የይዞታ ወይም የባለቤትነት ወይም ሌላ ማንኛውም ክርክር፣ በከተማው ውስጥ ከሚገኝ እድር ጋር በተያያዘ የመዳኘት ሥልጣናቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በተጨማሪ በግለሰቦች መካከል የሚደረጉ እስከ ብር 500,000 (አምስት መቶ ሺህ ብር) የገንዘብ፣ ውል፣ እና ብድር ክርክሮች የሚመለከቱ ሆኖ ቀሪ በአዲስ አበባ እና ድሬዳዋ ከተሞች የሚነሱ የፍትሀብሄር ክርክሮች በፌዴራል ፍርድ ቤቶች የሚዳኙ ይሆናሉ፤

ጀ) በሌሎች ሕጎች የተጠቀሱ ጉዳዮች፡፡

፪/ የክልል ጉዳይ በክልሉ ፍርድ ቤት እየታየ እያለ ወይም ከተወሰነ በኋላ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፩ «ሸ» እና «ነ» ላይ የተጠቀሰ ተከራካሪ በማንኛውም ሁኔታ ወደ ክርክሩ ቢገባ እንኳ ጉዳዮ በክልሉ ፍርድ ቤት መታየቱ ይቀጥላል፡፡

## ፮. የፌደራል ፍርድ ቤቶች ስለሚሠሩባቸው መሠረታዊ ሕጎች

፩/ የፌደራል ፍርድ ቤቶች የሥልጣን ክልላቸውን መሠረት አድርገው የሚቀርቡ ጉዳዮችን ወይም ክርክሮችን ቀጥሎ የተጠቀሰውን መሠረት አድርገው ይዳኛሉ፡-

ሀ) ህገ መንግሥቱን ፣ የፌደራል መንግሥቱን ሕጎችና ኢትዮጵያ አባል የሆነችባቸዉን ዓለም አቀፍ ስምምነቶች፤

ለ) ጉዳዩ የክልል ፣የአዲስ አበባ ወይም ድሬዳዋ ከተሞችን ሕግ የሚመለከት ሆኖ ሲገኝ የክልሉን ወይም የከተማውን ሕግ ፡፡

m) cases arising out of patent, literary and artistic-ownership rights;

n) cases involving insurance policy;

o) application for habeas corpus;

p) Without prejudice to the Charter Proclamation provides for City Administration Courts civil jurisdiction, such as a document in accordance with the provisions of the Critical Event Registration and Identification Act, the issue of name change, disappearance, conviction, marital status, custody and guardian evidence or ownership of a house administered by the city administration. Or any other dispute, subject to the jurisdiction of the city association, additionally civil disputes of money contracts, and loans between individuals up to Birr 500,000 (Five Hundred Thousand Birr), are under their jurisdiction. and the remaining civil disputes in Addis Ababa and Dire Dawa will be adjudicated in Federal Courts;

q) cases specified by other laws.

2/ A regional matter shall continue to be heard by regional court even where a party mentioned under Sub-Article (1)(g) and (n) of this Article intervenes under any condition in the proceeding or after judgment.

## 6. Substantive Laws to be Applied by Federal Courts

1/ Federal Courts shall settle cases or disputes, submitted to them within their jurisdiction on the basis of:

a) the Constitution, Federal Laws and International Treaties to which Ethiopia is a party;

b) Regional; Addis Ababa or Dire Dawa city laws where the case relates to same.

lawyer.et



**፯. የፌደራል ፍርድ ቤቶች ስለሚሠሩባቸው የሥነ ሥርዓት ሕጎች**

በሥራ ላይ ያሉ የወንጀል እና የፍትሐ ብሔር ሥነ-ሥርዓት ሕጎች ከዚህ አዋጅ ጋር እስካልተቃረኑ ድረስ እንዲሁም ሌሎች አግባብነት ያላቸው ሕጎች በዚህ አዋጅ ባልተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት ይኖራቸዋል፡፡

## ምዕራፍ ሦስት

## ስለ ፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን

**፰. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን**

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚከተሉት ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል፦

፩/ በሕግ በሚወሰነው መሠረት አንድ ጉዳይ ከአንድ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ችሎት ወደ ሌላ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ችሎት ወይም በውክልና ለክልል ፍርድ ቤቶች የተሰጡ የፌደራል ጉዳዮችን በሚመለከት ከክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት ወደ ፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንዲዛወር በሚቀርብ ጥያቄ፤ እና

፪/ በሌሎች ህጎች በተጠቀሱ ጉዳዮች።

**፱. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የይግባኝ የዳኝነት ሥልጣን**

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሚከተሉትን ጉዳዮች በይግባኝ የማየት ሥልጣን ይኖረዋል፦

፩/ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣኑ ውሣኔ የሰጠባቸው፣

፪/ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ ሰሚነት ሥልጣኑ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ከሰጠው ውሳኔ የተለየ ውሳኔ የሰጠባቸው ፣

፫/ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፌደራል ጉዳዩችን በተወካይነቱ በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑ አይቶ ውሳኔ የሰጠባቸው፣

፬/ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፌደራል ጉዳዮችን በተወካይነቱ በይግባኝ ሰሚነት ሥልጣኑ የክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከሰጠው ውሳኔ የተለየ ውሳኔ የሰጠባቸው፣

፭/ በሌሎች ሕጐች የተጠቀሱ ጉዳዮችን፡፡

**7. Procedural Laws to be Applied by Federal Courts**

The Criminal and Civil Procedure Codes as well as other relevant laws in force shall apply with respect to matters not provided for under this Proclamation insofar as they are not inconsistent therewith.

## CHAPTER THREE

## JURISDICTION OF THE FEDERAL SUPREME COURT

**8. First Instance Jurisdiction of the Federal Supreme Court**

The Federal Supreme Court shall have :

1/ first instance jurisdiction over application lodged in accordance with the law for change of venue from one Federal High Court Division to another Federal High Court Division or from Regional Supreme Court to Federal High Court regarding federal matters referred to Regional Courts by delegation; and

2/ Cases specified by other laws.

**9. Appellate Jurisdiction of the Federal Supreme Court**

The Federal Supreme Court shall have appellate jurisdiction over the following cases:

1/ Decisions of the Federal High Court rendered in its first instance jurisdiction;

2/ Decisions of the Federal High Court rendered in its appellate jurisdiction in variation of the decisions of the Federal First Instance Court;

3/ Decisions rendered by Regional Supreme Court on federal matters in its first instance jurisdiction in exercising its delegation;

4/ Decisions rendered by Regional Supreme Court on federal matters on its appellate jurisdiction in variation of the decision of the Regional High Court, exercising its delegation;

5/ Cases specified by other laws.

lawyer.et



## ፲. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሰበር ሥልጣን

፩/ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስሕተት ያለባቸውን የሚከተሉትን ጉዳዮች በሰበር የማየት ሥልጣን ይኖረዋል፦

ሀ) የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በይግባኝ አይቶ የመጨረሻ ውሳኔ የሰጠባቸው ፤

ለ) የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት የመጨረሻ ውሣኔ የሰጠባቸው፤

ሐ) የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፬)(ሀ) እና (ሸ) ን በተመለከተ የመጨረሻ ውሳኔ የሰጠባቸው፣

መ) የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፬) (ለ) በተመለከተ የመጨረሻ ውሳኔ የሰጠባቸው እና ጉዳዮቹ ለህዝብ ጥቅም ሀገራዊ ፋይዳ ያላቸዉ ሲሆኑ፤

ሠ) የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ወይም የየክልሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤቶች በሀገ መንግስቱ በተሰጣቸዉ የዉክልና ስልጣን የፌደራል ጉዳይን አይተዉ የመጨረሻ ዉሳኔ የሰጡበት፤

ረ) የአዲስ አበባ ወይም የድሬዳዋ ከተማ ፍርድ ቤት የመጨረሻ ውሳኔ የሰጠባቸው ፤

ሰ) በሕግ የመዳኘት ሥልጣን በተሰጠው አካል ወይም በሌሎች አካላት የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ ፤

ሸ) አግባብነት ያላቸው የህግ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆነዉ ፤ በፌደራል ፍርድ ቤት ሊታይ ይችል በነበረ ጉዳይ ላይ በአማራጭ የክርክር መፍቻ ዘዴዎች መሠረት የተሰጠ የመጨረሻ ውሳኔ፤

ቀ) በሌሎች ሕጎች የተጠቀሱ ጉዳዮች፡፡

፪/ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከአምስት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት የሰበር ሰሚ ችሎት የሚሰጠው የሕግ ትርጉም ውሳኔው ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በየትኛዉም ደረጃ በሚገኝ የፌደራልም ሆነ የክልል ፍርድ ቤት አስገዳጅነት ይኖረዋል፡፡

፫/ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሰበር ችሎቶች አስገዳጅ የሕግ ትርጉም የተሰጠባቸውን ውሳኔዎች በኤሌክትሮኒክስ ወይም በህትመት ሚዲያዎች በተቻለ ፍጥነት ያሰራጫል።

## 10. Power of Cassation of the Federal Supreme Court

1/ The Federal Supreme Court shall have the power of cassation over the following cases when they contain basic or fundamental error of law:

a) final decisions of the Federal High Court rendered in its appellate jurisdiction;

b) final decisions of the Federal Supreme Court Appellate Division;

c) final decisions of Regional Supreme Court Cassation Division regarding cases mentioned under Article 2 Sub – Articles(4)(a) and (h) of this Proclamation;

d) final decisions of Regional Supreme Court Cassation Division regarding cases mentioned under Article 2 Sub – Articles(4)(b) of this Proclamation and when these cases have public interest and national importance;

e) final decisions of regional high court or supreme court on federal matters while exercising their constitutionally delegated power of adjudication;

f) final decisions of the highest level of Addis Ababa or Dire Dawa City Court;

g) final decision rendered by organ vested with judicial power or other bodies;

h) without prejudice to the provisions of appropriate law, final decision rendered by an alternative dispute resolution mechanisms regarding case that may be filed in federal court;

i) cases specified by other laws.

2/ Interpretation of law rendered by the Cassation Division of the Federal Supreme Court with not less than five judges shall be binding from the date the decision is rendered.

3/ The Federal Supreme Court shall publicize decisions rendered by its Cassation Divisions on binding interpretation of laws by electronics and print Medias as soon as possible.

lawyer.et



## ምዕራፍ አራት
## ስለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የዳኝነት ሥልጣን

### ፲፩. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ የፍትሐ ብሔር የዳኝነት ሥልጣን

፩/ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ግምታቸዉ ከብር አስር ሚሊዮን (፲ ሚሊዮን ብር) በላይ በሆኑ በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል፡-

ሀ) የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፬ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፫ እና ፭ መሰረት በሚነሱ ማናቸዉም የፍትሀብሄር ጉዳዮች፤

ለ) በአዲስ አበባ እና በድሬዳዋ በሚነሱ ማናቸዉም የፍትሀብሄር ጉዳዮች፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩)(ሀ) ቢኖርም፣ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሚከተሉት የፍትሐ ብሔር ጉዳዮች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል፡-

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ ንዑስ አንቀጽ (፩)(ሀ) እስከ ንዑስ አንቀጽ (፩)(ሠ) ላይ በተጠቀሱት የፍትሐብሔር ጉዳዮች፤

ለ) በሕግ በሚወሰነው መሠረት አንድን ጉዳይ ከአንድ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ችሎት ወደ ሌላ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ችሎት ወይም ወደ ራሱ እንዲዛወር የሚቀርብን ጥያቄ፤

ሐ) በሌሎች ህጎች የተጠቀሱ ጉዳዮች፡፡

፫/ በዚህ አዋጅ ሌሎች ድንጋጌዎች እንዲሁም በሌሎች ህጎች የተመለከተዉ ቢኖርም የፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት በፍርድ ታይተዉ ሊወሰኑ የሚችሉ በህገ መንግስቱ ምዕራፍ ሶስት ስር የተመለከቱ መሰረታዊ መብቶች እና ነጻነቶችን ለማስከበር ለጉዳዩ ተገቢ የሆነ ፍርድ፣ትዕዛዝ ወይም ዉሳኔ የመስጠት ስልጣን አለዉ።

፬/ ማንኛዉም በጉዳዩ ላይ መብት ወይም ጥቅም ያለዉ ሰዉ ወይም ጉዳዩን ለማቅረብ በቂ ምክንያት ያለዉ ሰዉ መሰረታዊ መብቶች እና ነጻነቶችን ለማስከበር ለፌደራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቤቱታ ማቅረብ መብት አለዉ።

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) እና (፬) የተጠቀሰ ጉዳይን ለማስተናገድ ፍርድ ቤቱ የፍትሀብሄር ሥነ-ሥርዓት ህግ ቁጥር ከ ፩፻፸፮ እስከ ፩፻፸፱ እንደአግባብነቱ ሊጠቀም ይችላል፡፡

## CHAPTER FOUR
## JURISDICTION OF THE FEDERAL HIGH COURT AND THE FEDERAL FIRST INSTANCE COURT

### 11. First Instance Civil Jurisdiction of the Federal High Court

1/ The Federal High Court shall have first instance jurisdiction over the following civil cases involving an amount exceeding Birr 10,000,000 (Ten Million Birr);

a) Without prejudice to Article 14 of this Proclamation, any federal civil cases arising under Articles 3 and 5 of this Proclamation;

b) Civil cases arising in Addis Ababa and Dire Dawa.

2/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) (a) of this Article, the Federal High Court shall have first instance jurisdiction over the following civil cases፡

a) Cases specified under Sub-Article (1) (a) to – (e) of Article 5 of this Proclamation;

b) Application for change of venue from one Federal First Instance Court Division to another Federal First Instance Court Division or to itself, in accordance with the law; and

c) Cases specified by other laws.

3/ Notwithstanding the provisions of this proclamation and other relevant laws, the Federal High Court may render decision, judgement or order in order to protect justiciable human rights specified under chapter three of the Constitution.

4/ Any person who has vested interest or sufficient reason may institute a suit before the Federal High Court to protect the rights of his own or others.

5/ The court may use as appropriate Article 176-179 of the civil procedure code for any proceedings mentioned under Sub-Article (3) and (4) of this Article.

lawyer.et



**፲፪. ፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የመጀመሪያ ደረጃ የወንጀል የዳኝነት ሥልጣን**

የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በሚከተሉት የወንጀል ጉዳዮች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል፦

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፫ እና ፬ ላይ የተመለከቱና አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት ለከፍተኛ ፍርድ ቤት በተሰጡ በፌደራል የወንጀል ጉዳዮች፤

፪/ በአዲስ አበባ ወይም በድሬዳዋ ከተሞች ውስጥ በሚነሱና አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት ለከፍተኛ ፍርድ ቤት በሚቀርቡ በሌሎች የወንጀል ጉዳዮች፤ እና

፫/ በሌሎች ሕጎች ለፌደራል ፍርድ ቤት በተሰጡ የወንጀል ጉዳዮች፡፡

**፲፫. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የይግባኝ ዳኝነት ሥልጣን**

የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሚከተሉትን የፍትሐብሔር እና የወንጀል ጉዳዮች በይግባኝ የማየት ሥልጣን ይኖረዋል፦

፩/ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የሰጠውን ውሳኔ፤ እና

፪/ በሌሎች ሕጎች የተጠቀሱ ጉዳዮችን፡፡

**፲፬. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የፍትሐ ብሔር ዳኝነት ሥልጣን**

የዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፩ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሚከተሉት ጉዳዮች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የፍትሐብሔር የዳኝነት ሥልጣን አለው፦

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፫ እና ፭ መሠረት በሚቀርቡ የፌደራል የፍትሐ ብሔር ጉዳዮች፤

፪/ በሕግ ለሌሎች አካላት የተሰጠው የዳኝነት ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ፤ በአዲስ አበባ ወይም በድሬዳዋ ከተማ ውስጥ በሚነሱ ሌሎች የፍትሐ ብሔር ጉዳዮች፣ እና

፫/ በሌሎች ሕጎች የተጠቀሱ የፍትሀብሄር ጉዳዮች፡፡

**፲፭. የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የወንጀል የመጀመሪያ የዳኝነት ሥልጣን**

በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፪ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የተሰጠው ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ ፤ የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት በሚከተሉት የወንጀል ጉዳዮች ላይ የመጀመሪያ ደረጃ የዳኝነት ሥልጣን ይኖረዋል፦

**12. First Instance Criminal Jurisdiction of the Federal High Court**

The Federal High Court shall have first instance jurisdiction over the following criminal cases:

1/ Federal criminal cases mentioned under Article 3 and 4 of this Proclamation and falling under the jurisdiction of the High Court pursuant to appropriate laws;

2/ Other criminal cases arising in the cities of Addis Ababa or Dire Dawa and falling under the jurisdiction of the High Court pursuant to appropriate laws; and

3/ Criminal cases given to Federal court by other laws.

**13. Appellate Jurisdiction of the Federal High Court**

The Federal High Court shall have appellate jurisdiction over the following:

1/ on decision of the Federal First Instance Court; and

2/ cases specified by other laws.

**14. Civil Jurisdiction of the Federal First Instance Court**

Without prejudice to Article 11 of this Proclamation, the Federal First Instance Court shall have jurisdiction over the following civil cases:

1/ Federal civil cases submitted pursuant to Article 3 and 5 of this Proclamation;

2/ Without prejudice to judicial power vested in other organs by law, other civil cases arising in Addis Ababa or Dire Dawa Cities; and

3/ Civil cases specified by other laws.

**15. Criminal Jurisdiction of the Federal First Instance Court**

Without prejudice to the jurisdiction of the Federal High Court under Article 12 of this proclamation, the Federal First Instance Court shall have jurisdiction over the following criminal cases:

lawyer.et



፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፫ እና ፬ ላይ የተመለከቱና አግባብነት ባላቸው ሕጎች መሠረት ለከፍተኛ ፍርድ ቤት የማይቀርቡ በፌደራል የወንጀል ጉዳዮች፤

፪/ በሕግ ለሌሎች አካላት የተሰጠው የዳኝነት ሥልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ፣ በአዲስ አበባ ወይም ድሬዳዋ ከተሞች ውስጥ በሚነሱ እና በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፪ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በማይታዩ ሌሎች የወንጀል ጉዳዮች፣ እና

፫/ በሌሎች ሕጎች የተጠቀሱ ጉዳዮች፡፡

1/ Federal criminal cases mentioned under Article 3 and 4 of this Proclamation and not referred to the High Court pursuant to appropriate laws;

2/ Without prejudice to judicial power vested in other organs by law, other criminal cases arising in the cities of Addis Ababa or Dire Dawa not falling under the jurisdiction of the Federal High Court as mentioned under Article 12 Sub- Article (2); and

3/ Cases specified by other laws.

### ፲፮. <u>የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት የይግባኝ ስልጣን</u>

የፌደራል መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት አግባብነት ባላቸዉ ህጎች በግልጽ በተሰጡት ጉዳዮች ላይ በይግባኝ የማየት ስልጣን ይኖረዋል።

### 16. <u>Appellate Jurisdiction of Federal First Instance Court</u>

Federal first instance court shall have an appellate jurisdiction on matters specifically bestowed on it by relevant laws.

## <u>ምዕራፍ አምስት</u>

## <u>ስለ ፌደራል ፍርድ ቤቶች ፕሬዚዳንቶች፣ ም/ፕሬዚዳንቶች፣የምድብ ችሎት ተጠሪ ዳኞች እና ሰብሳቢ ዳኞች</u>

## <u>CHAPTER FIVE</u>

## <u>THE PRESIDENTS, VICE-PRESIDENTS, ASSIGNED DIVISIONS REPRESENTATIVE JUDGES AND PRESIDING JUDGES OF FEDERAL COURTS</u>

### ፲፯. <u>የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ሥልጣንና ተግባር</u>

፩/ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት በሕግ መሠረት የፌደራል ፍርድ ቤቶችን ለማስተዳደር ኃላፊ ይሆናል፡፡

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) አጠቃላይ አነጋገር እንደተጠበቀ ሆኖ ፤ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ቀጥሎ የተጠቀሱት ስልጣን እና ተግባራት ይኖሩታል፦

ሀ) ለፌደራል ዳኝነት አስተዳደር ጉባዔ የተሰጠው ሥልጣንና ተግባር እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የፌደራል ፍርድ ቤት ዳኞችን፣ የምድብ ችሎቶች ተጠሪ ዳኞችን እና ሰብሳቢ ዳኞችን ይደለድላል ፣ ሥራ ይሰጣል፣

ለ) ለፌደራል ፍርድ ቤቶች አስፈላጊ የሆኑ ሠራተኞችን ይቀጥራል፣

ሐ) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(፪)(ሠ) ላይ የተጠቀሰውን ጨምሮ የፌደራል ፍርድ ቤቶችን ዕቅድና በጀት አዘጋጅቶ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያቀርባል፣ ሲፀድቅም ሥራ ላይ ያውላል፣

### 17. <u>Powers and Duties of the President of the Federal Supreme Court</u>

1/ The President of the Federal Supreme Court shall be responsible for the administration of Federal Courts in accordance with the law.

2/ Without prejudice to the generality of Sub-Article (1) of this Article, the President of the Federal Supreme Court shall:

a) without prejudice to the power and duty entrusted to the Federal Judicial Administration Council, place and assign judges of Federal Courts, Representative Judges of Assigned Divisions and Presiding Judges;

b) employ personnel necessary for Federal Courts;

c) prepare and submit to the House of People's Representatives the work plan and budget of Federal Courts including those mentioned under Sub-Article(2) (e) of this Article and implement same upon approval;

lawyer.et



መ) በዚህ አዋጅ ላይ በተጠቀሰው መሠረት በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መውጣት ያለባቸው ደንቦች እና መመሪያዎች እንዲዘጋጁና እንዲወጡ በማድረግ ተግባራዊ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

ሠ) የፌደራል ፍርድ ቤቶችን የዳኝነት ሥልጣን በውክልና ለሚሰሩ የክልል ፍርድ ቤቶች የበጀት ማካካሻ ጥያቄ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፤

ረ) የክልል ፍርድ ቤቶች የፌደራል ጉዳዮችን አስመልክቶ በውክልና ስላከናወኑት ተግባር በስታስቲክስ የተደገፈ ሪፖርት ተዘጋጅቶ እንዲቀርብ ያደርጋል፣

ሰ) የዳኞችና የሌሎች ሠራተኞች ትምህርትና ሥልጠና የሚካሄድበትን ሁኔታ እንደአስፈላጊነቱ ያመቻቻል፣

ሸ) በክልል ስለሚታዩ የፌደራል ጉዳዮች የመዝገብ አያያዝና ጠቅላላ አሠራር ከክልል ፍርድ ቤቶች ጋር በመመካከር የሚሻሻልበትን ሁኔታ ያመቻቻል፣

ቀ) ስለ ፌደራል ፍርድ ቤቶች የበጀት አፈጻጸም ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሪፓርት ያቀርባል፣

በ) የፌደራል ፍርድ ቤቶች ፍርድ አፈፃፀም ተቋም ፣ የተከላካይ ጠበቆችን ቢሮ እና በሕግ ለፌደራል ፍርድ ቤቶች የተሰጡ ተግባራትን ለማስፈፀም የሚያስችሉ የሥራ ክፍሎች እንዲደራጅ ያደርጋል፤

ተ) የፌደራል ፍ/ቤቶች ዳኞች ስልጠና መመሪያ ያወጣል፤

ቸ) ለኢትዮጵያ የዳኝነት ሥርዓት እድገት፤ ቀልጣፋ አሰራር እና ውጤታማነት የሚያግዙ ጥናቶች እንዲካሄዱ ያደርጋል፤ተግባራዊነታ ቸውን ይከታተላል፤

ነ) የፌደራል ሸሪአ ፍርድ ቤቶች በተቋቋሙበት አዋጅ መሠረት የዳኝነት ሥራቸውን እንዲያከናውኑ ድጋፍ ይሰጣል፤

ኘ) በሕግ እና በዚህ አዋጅ የተሰጡ ሌሎች ተግባሮችን ያከናውናል፡፡

d) ensure preparation, issuance and implementation of Regulations and directives to be issued by the Federal Supreme Court as provided under this Proclamation;

e) decide upon requests for budgetary subsidy to Regional Courts exercising federal jurisdiction by delegation;

f) causes the preparation and the submission of reports on the activities of Regional Courts concerning Federal cases, as supported by statistical data;

g) facilitate conditions for the education and training of judges and other personnel as may be necessary;

h) in consultation with Regional Courts, work out ways for improving the records of management and general practices of the courts as relating to the cases;

i) submit to the House of Peoples Representatives reports on the budget implementation of the Federal Courts;

j) organize the Federal Courts decisions execution body; public defense office and offices that will enable Federal Courts execute duties entrusted to them by law;

k) issue directives on training of federal judges;

l) cause studies to be conducted for institutional development, modernized efficient operations and effectiveness of the Ethiopian judicial system and ensure their implementation;

m) provide support to Federal Sharia Courts in exercising their judicial work in accordance with the establishment Proclamation; and

n) perform other duties entrusted by law and this Proclamation.

lawyer.et



**፲፰. <u>የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት ሥልጣንና ተግባር</u>**

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንት የሚከተሉት ስልጣን እና ተግባር ይኖሩታል፦

፩/ በፕሬዚዳንት የሚመራለትን ሥራ ማከናዎን፣

፪/ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት በማይኖርበት ጊዜ ፕሬዚዳንቱን ተክቶ መስራት፡፡

**፲፱. <u>ስለ ፌደራል ከፍተኛ እና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንቶች ሥልጣንና ተግባር</u>**

፩/ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት የመምራት እና ክትትል የማድረግ ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የየፍርድ ቤቱ ፕሬዚዳንቶች፦

ሀ) ፍርድ ቤቱን ይወክላሉ፤

ለ) የፍርድ ቤቱን ዳኞች ይደለድላሉ፣ ሥራ ይሰጣሉ፣ ያስተዳድራሉ፤

ሐ) የፍርድ ቤቱን የአስተዳደር ሠራተኞች ያስተዳድራሉ፤

መ) የየፍርድ ቤቱን ፋይናንስ ያስተዳድራሉ፤

ሠ) በሕግ እና በዚህ አዋጅ የተሰጡ ሌሎች ተግባራትን ያከናውናሉ፤

ረ) በፍርድ ቤቱ የሚሰጡ አገልግሎቶች ተገማች፣ ቀልጣፋ እና ግልፅ የሚሆኑበትን አሰራር ይዘረጋሉ፤ስለተፈፃሚነቱም ክትትል ያደርጋሉ፤

ሰ) የፆታ ጥቃት የተፈፀመባቸው ሴቶች፤ ህፃናት፤ አካልጉዳተኞችና አረጋዊያንን አስመልክቶ በፍርድ ቤቶች የሚከፈቱ መዝገቦች በተፋጠነ ፍትህ አገልግሎት እልባት እንዲያገኙ እና የህግ ባለሙያ ድጋፍ እንዲሰጣቸው ያደርጋሉ፡፡

፪/ የፍርድ ቤቱን ዕቅድና በጀት አዘጋጅተው ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ያቀርባሉ ፣ ሲፈቀድም ሥራ ላይ ያውላሉ፣ ይህንም የሚቆጣጠሩበት የኦዲት ሥርዓት ይኖራቸዋል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) የታቀዱ ስራዎች ቀልጣፋ እና ዉጤታማ በሆነ መንገድ እንዲከናወኑ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚዘረጋዉ የተጠያቂነት ስርዓት የሚመዘን ይሆናል።

**18. <u>Power and Duties of the Vice-President of the Federal Supreme Court</u>**

The Vice-President of the Federal Supreme Court shall have the following powers and duties:

1/ Discharge the duties assigned to him by the President;

2/ Serve in the President's stead, while he is absent.

**19. <u>Powers and Duties of the Presidents of the Federal High Court and First Instance Court</u>**

1/ Without prejudice to the Suprim Court president's power to supervise and lead the courts, presidents of the first instance court and high court shall:

a) Represent the court;

b) Place, assign and administer judges of the court;

c) administer personnel of the court;

d) administer finance of Court;

e) Perform other duties entrusted by law and this Proclamation;

f) Establish feasible, fast and transparent Court service system and follow up its implementation;

g) Facilitate with rapid court decision and professional support to court causes of victim women, children, disability persons and old ages.

2/ prepare and submit to the Federal Supreme Court the work plan and budget of the court and implement same upon approval as well may have Audit system to control same.

3/ The effectiveness and efficiency of work plans prepared pursuant to Sub-Article (2) of this Article shall be evaluated as per the Federal Supreme Courts accountability system.

፬/ የፍርድ ቤቱን የእቅድና በጀት አፈፃፀም በየሩብ ዓመቱ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሪፖርት ያቀርባል፡፡

፭/ የፌደራል የከፍተኛና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች የየራሳቸው ምክትል ፕሬዚዳንቶች ይኖሯቸዋል፡፡

፮/ የየፍርድ ቤቱ ምክትል ፕሬዚዳንቶች የፍርድ ቤቱ ፕሬዚዳንት በማይኖርበት ጊዜ በመተካት ይሰራሉ፤እንዲሁም በፕሬዚዳንቱ የሚሰጡ ሌሎች ሥራዎች ያከናውናሉ።

፯/ የፌደራል ከፍተኛ እና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች ፕሬዚዳንቶች እና ምክትል ፕሬዚዳንቶች በፍርድ ቤቶቻቸው በሚገኙ ማናቸውም ችሎቶች ሰብሳቢ ዳኛ ሆነው ሊያስችሉ ይችላሉ።

## ፳. የፌደራል ከፍተኛ እና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ምክትል ፕሬዚዳንቶች ሥልጣንና ተግባር

፩/ የፍርድ ቤቱ ፕሬዚዳንቶች በሌሉበት ጊዜ ተክተው ይሰራሉ፡፡

፪/ የፍርድ ቤቱ ፕሬዚዳንቶች የሚሰጧቸውን ሥራ ይሰራሉ፡፡

## ፳፩. ስለ ምድብ ችሎት ተጠሪ ዳኛ ሥልጣንና ተግባር

፩/ የፌደራል ከፍተኛ እና መጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች በሚያስችሉበት ምድብ ችሎቶች የየራሳቸዉ ተጠሪ ዳኛ ይኖራቸዋል፡፡

፪/ የየምድብ ችሎቶቹ ተጠሪ ዳኞች ከዳኝነት ሥራ በተጨማሪ ከየፍርድ ቤቶች ፕሬዚዳንቶች በሚሰጧቸዉ የስራ መመሪያ መሰረት የሚከተሉትን ተግባራት ያከናዉናሉ፦

ሀ) የምድብ ችሎቶቹን ሥራ ማስተባበር፤

ለ) ለሚቀርቡ አስተደደራዊ ቅሬታዎች ምላሽ መስጠት፣ ሠራተኞችን ማስተዳደር፤

ሐ) በምድብ ችሎቶቹ ስለተከናወኑ ሥራዎች ለየፍርድ ቤታቸው ፕሬዚዳንት ሪፓርት ማቅረብ፣

መ) የየፍርድ ቤቱ ፕሬዚዳንት የሚሰጧቸዉን ሌሎች ተግባራት ማከናዎን፡፡

፫/ የፍርድ ቤቱ ፕሬዚዳንት በሚሰጣቸዉ ዉክልና መሰረት የምድብ ችሎቱን ፋይናንስ ማስተዳደር።

4/ submit plan and budget performance report quarterly to federal supreme court.

5/ The Federal High Court and First Instance Court shall have their respective Vice-Presidents.

6/ The Vice-President of each court shall serve in the President's stead in the absence of the President and discharge other duties as may be assigned by the President.

7/ Presidents and Vice Presidents of Federal High and First Instance Courts may be assigned as a presiding judge in any division of their respective Courts.

## 20. Powers and Duties of Vice Presidentes of the Federal High Court and First Instance Court

1/ on the absence of the president shall serve in the stead.

2/ perform duties assigned to them by the presidents.

## 21. Powers and Duties of Representative Judge of an Assigned Division

1/ Divisions of Federal High Court and First Instance Court shall have their own representative judge.

2/ Representative Judges of each Assigned Divisions shall, in addition to its judicial function, perform the following activities by the direction of their respective Court Presidents:

a) Coordinate works of the Assigned division;

b) Provide proper response to complaints related to administrative matters and administer employees;

c) Submit report to their respective court president regarding works conducted in the Assigned Division;

d) Perform other duties as may be entrusted by their respective court president.

3/ Administer the finance of assigned division based on the delegation from the president of their respective court.

lawyer.et



**፳፪. ስለ ፌደራል ፍርድ ቤት የችሎት ሰብሳቢ ዳኛ**

ሶስትና ከሶስት በላይ የሆኑ ዳኞች በሚያስችሉበት የፌደራል ፍርድ ቤት ችሎት ሰብሳቢ ዳኛ ይኖረዋል፡፡

**፳፫. የፌደራል ፍርድ ቤት ችሎት ሰብሳቢ ዳኛ ተግባር**

፩/ የፌደራል ፍርድ ቤት ችሎት ሰብሳቢ ዳኛ የሚከተሉትን ተግባራት ያከናዉናል፡-

ሀ) የችሎቱ ሥራ በህግ መሠረት መመራቱን በማረጋገጥ ችሎቱን ማስተዳደር፤

ለ) በችሎቱ የሚወሰኑ መዝገቦች በሁሉም የችሎቱ ዳኞች ግንዛቤ የተወሰደባቸው መሆኑን ማረጋገጥ፤

ሐ) ለችሎቱ የተመደቡ የአስተዳደር ሰራተኞችን ማስተዳደር፤13241

መ) ሁሉም የችሎቱ ዳኞች በችሎቱ የሚሰጡ ውሳኔዎችን በማዘጋጀት ተመጣጣኝ ተሳትፎ ማድረጋቸውን መከታተል፡፡

፪/ ሰብሳቢ ዳኛው በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከቱትን ተግባራት የችሎቱን ዳኞች የዳኝነት ነፃነት በማይጋፋ ሁኔታ ይፈጽማል፡፡

**ምዕራፍ ስድስት**

**ስለ ፌደራል ፍርድ ቤቶች አደረጃጀትና የዳኝነት ሥራ አካሄድ**

**፳፬. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች፣ ሌሎች ባለሙያዎች እና የአስተዳደር ሠራተኞች**

፩/ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አንድ ፕሬዚዳንት፣ አንድ ምክትል ፕሬዚዳንት እንዲሁም የዳኝነት ስራዉን ለማከናዎን አስፈላጊ የሆኑ ዳኞች ይኖሩታል፡፡

፪/ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት አዋጁን ለማስፈፀም በሚወጣው ደንብ መሠረት የሚያስተዳድራቸው የፌደራል ፍርድ ቤቶች ዳይሬክተሮች፣ ሬጅስትራሮች፣ ረዳት ዳኞች፣ የህግ ባለሙያዎች እና ሌሎች ሠራተኞች ይኖሩታል፡፡

**22. Presiding Judge of the Federal Courts**

A Federal Court division in which three or more judges are sitting shall have a presiding judge.

**23. Duties of the Presiding Judge of Federal Courts**

1/ The Presiding Judge of the division of Federal Courts shall undertake the following functions:

a) Administer the overall tasks of the division by ensuring that the process of the division is conducted in accordance with the law;

b) Ensure that each judge of the division has clear awareness about the content of each file decided by the Division;

c) Administer administrative workers of the division;

d) Ensure proportional participation of each judge of the division in preparing judgement and/or decisions rendered by the division.

2/ The Presiding Judge shall conduct the duties mentioned in Sub-Article (1) of this Article without impairing judicial independence of judges of the Division.

**CHAPTER SIX**

**FEDERAL COURT STRUCTURE AND THE ADMINISTRATION OF JUSTICE**

**24. Judges, Other Professionals and Administrative workers of the Federal Supreme Court**

1/ The Federal Supreme Courts shall have a President, a Vice-President and Judges necessary for adjudication.

2/ The Federal Supreme Court shall have Federal Courts directors, registrars, assistant judges, legal experts and other support staff inaccordance with regulation issued to implement the Proclamation.

lawyer.et



**፳፭. የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ችሎቶች**

፩/ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለሥራው አስፈላጊ የሆኑ የፍትሀብሄር እና የወንጀል የመጀመሪያ ደረጃ፣ ይግባኝ ሰሚ እና ሰበር ሰሚ ችሎቶች ይኖሩታል፡፡

፪/ በእያንዳንዱ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ሰሚ ችሎት ከ፫ (ሶስት) ባላነሱ ዳኞች የሚያስችሉ ሲሆን የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎቶች ደግሞ ከ ፭ (አምስት) ባላነሱ ዳኞች ያስችላሉ፡፡

፫/ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት እና ምክትል ፕሬዚዳንት በጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚገኙ ማንኛዉም ችሎት ሰብሳቢ ዳኛ ሆነው ሊያስችሉ ይችላሉ፡፡

**፳፮. ከሰባት ያላነሱ ዳኞች ስለሚሰየሙበት የሰበር ችሎት**

፩/ አምስት ዳኞች የተሰየሙበት የሰበር ችሎት በባለጉዳዮቹ አመልካችነት ወይም በችሎቱ በራሱ አነሳሽነት ቀድሞ የተሰጠዉን አስገዳጅ የህግ ትርጉም በተለያዩ ምክንያቶች ማሻሻል አስፈላጊ ሆኖ ካገኘዉ ከሰባት ያላነሱ ዳኞች በተሰየሙበት የሰበር ችሎት እንዲታይ በቂ እና አሳማኝ ምክንያቶችን ተንትኖ በመግለጽ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ማቅረብ ይችላል።

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተገለጸዉ መሰረት ጥያቄ ሲቀርብለት የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፕሬዚዳንት ከሰባት ያላነሱ ዳኞች በሚሰየሙበት የሰበር ችሎት ጉዳዩ እንዲታይ ያደርጋል።

፫/ በዚህ አንቀጽ የተገለጸዉ የሰበር ችሎት የሚሰጠዉ የህግ ትርጉም ዉሳኔዉ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ በማንኛዉም ደረጃ ለሚገኝ የፌደራል ወይም የክልል ፍርድ ቤት አስገዳጅ ይሆናል።

፬/ በዚህ አንቀጽ መሰረት ከሰባት ያላነሱ ዳኞች የተሰየሙበት የሰበር ችሎት ቀድሞ የሰጠዉን የህግ ትርጉም ከሰባት ባላነሱ ዳኞች በተመሳሳይ ጭብጥ በሌላ ጊዜ ሊሻሻል ይችላል።

**፳፯. የሰበር አቤቱታ አቀራረብ ሥነ ሥርዓት**

፩/ ለሰበር ችሎት የሚቀርብ የሰበር ማመልከቻ በውሳኔው ላይ የተፈፀመውን መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፬) ላይ ከተሰጠው ትርጉም አንፃር ተገናዝቦና የሚጠየቀውን ዳኝነት በሚገልፅ መልኩ እና የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት

**25. Division of the Federal Supreme Court**

1/ The Federal Supreme Court shall have first instance, appellate and cassation divisions necessary for its function.

2/ Each Federal Supreme Court Appellate Division shall sit with not less than 3(three) judges and the Cassation Divisions shall sit with not less than 5(five) judges.

3/ President and Vice President of Federal Supreme Court may be assigned as a presiding judge in any division of their respective Courts.

**26. Cassation Division Sitting with not less than Five Judges**

1/ The cassation division presided by five judges may, by its own initiation or by a petition filed by one of the litigant parties, direct the case to be heard by a cassation division comprising of not less than seven judges by giving clear and sufficient reasons where changing the previous legal interpretation is so necessary.

2/ The president shall order that the case be heard by a cassation division presided by not less than seven judges, where a request has been made in accordance with Sub-Article (1) of this Article.

3/ Interpretation of law rendered by the cassation division pursuant to Sub-Article (1) of this Article shall be binding on all level of Federal and Reginal Courts from the date of the decision rendered.

4/ Interpretation of law rendered by cassation division presided by not less than seven Judges may review with the same issue by not less than seven Judges.

**27. Application Procedure for Cassation.**

1/ An application for a hearing in cassation shall state in short the reasons for alleging that the decision contains basic or fundamental error of law in line with the definition given under Sub – Article (4) of Article 2 of this Proclamation by stating the

lawyer.et



ይህን በተመለከተ በሚያወጣው መመሪያ መሠረት በአጭሩ ተፅፎ መቅረብ አለበት፡፡

፪/ የሚመለከተው አቤት ባይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተጠቀሰው መሠረት ከሚያቀርበው ማመልከቻ በተጨማሪ የሰበር አቤቱታ የቀረበበትን ውሣኔ እና የበታች ፍርድ ቤት ውሣኔ ቅጂዎችን ማቅረብ አለበት፡፡ ሆኖም የሰበር ችሎቱ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘዉ በስር ፍርድ ቤት ያለዉ ሙሉ መዝገብ ቅጅ እንዲቀርብለት ያደርጋል።

፫/ የሰበር ጥያቄ ማመልከቻ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት መቅረብ የሚገባው የሰበር ጥያቄ በሚቀርብበት ጉዳይ ላይ የመጨረሻ ውሣኔ ከተሰጠ ጀምሮ ባሉት ፺ (በዘጠና) ቀናት ውስጥ ይሆናል፡፡

## ፳፰. የሰበር አቤቱታን በሰበር ሰሚ ችሎት ስለማየት

፩/ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለሰበር ችሎት የሚቀርቡ ጉዳዮችን ክርክር አመራር ሥነ ሥርዓትን በተመለከተ የሚያወጣው ደንብ እንደተጠበቀ ሆኖ ፣ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲ መሠረት አቤቱታ በሰበር የሚሰማው አስቀድሞ ሶስት የጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች የተሰየሙበት ችሎት ውሳኔው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፪ ንዑስ አንቀጽ (፬) እና አንቀጽ ፲ ላይ በተመለከቱት መሠረት ለሰበር ችሎት መታየት አለበት ብሎ ሲወሰን ነው፡፡

፪/ የሰበር ችሎቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የተመራለትን ጉዳይ መርምሮ አቤቱታ በቀረበበት ጉዳይ ላይ የተፈፀመ መሠረታዊ የሆነ የሕግ ስህተት አለመኖሩን ከተረዳ አቤቱታውን ውድቅ በማድረግ ትዕዛዝ ይሰጣል፡፡

፫/ የሰበር ችሎቱ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሰረት የተመራለትን ጉዳይ መርምሮ አቤቱታ በቀረበበት ጉዳይ ላይ ያስቀርባል ብሎ ከተረዳ ጭብጥ በመያዝ በተጠሪ መልስ እንዲሰጥበት በአመልካች ከቀረበው የሰበር ማመልከቻ እና መጥሪያ ጋር ይልካል፡፡

፬/ ተከራካሪዎች መልስ እና የመልስ መልስ ክርክራቸውን በጽሁፍ አቅርበው ከተቀባበሉ በኋላ የሰበር ሰሚ ችሎቱ ተከራካሪዎችን መስማት ካላስፈለገው በስተቀር በጉዳዩ ላይ ውሳኔ ይሰጣል፡፡

requested relief and in accordance with the guideline issued by the Federal Supreme Court.

2/ The concerned applicant shall, in addition to the application submitted in accordance with Sub-Article (1) of this Article, submit a copy of the decision against which a cassation is lodged and of the decisions of lower courts. The cassation division may order the parties to bring the full copy of files from the lower courts.

3/ An application for a hearing in cassation shall be submitted to the Federal Supreme Court within 90 (ninety) days from the date on which the final decision protested against is rendered.

## 28. Petition and Proceedings in Cassation Division

1/ Without prejudice to regulation to be issued by the Federal Supreme Court regarding cases proceedings procedure of Cassation Division, the application shall be heard in cassation pursuant to Article 10 of this Proclamation subject to prior ruling as to the existence of fundamental or basic error of law qualifying for cassation as specified under Article 2 Sub-Article (4) of this Proclamation by a Division wherein three judges of the Federal Supreme Courts sit.

2/ When the Cassation Division to which the application is referred concludes upon examination of the application that there is no basic or fundamental error of law, it shall order the dismissal of the application.

3/ When the Cassation Division to which the application is referred concludes upon examination of the application that the case has a merit, it shall frame issue and send the same with the Cassation application and summon to the respondent to reply in writing.

4/ After submission of the written reply and counter reply and exchange of the same between the parties, the Cassation Division shall, unless it is necessary to hear the parties, render decision.

lawyer.et



**፳፱. የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች ዳኞች፣ ችሎቶችና ሌሎች ሠራተኞች**

፩/ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ለሥራቸው አስፈላጊ የሆኑ ዳኞችና ችሎቶች ይኖሯቸዋል፡፡

፪/ የፌደራል ከፍተኛ እና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፲፱ ንዑስ አንቀጽ (፩) (ለ) እና አንቀጽ ፳፫ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት የየፍርድ ቤቱ ፕሬዚዳንቶች የሚያስተዳድሯቸው ሬጅስትራሮች ፣ ረዳት ዳኞች ፣ የህግ ባለሙያዎች እና ሌሎች ሠራተኞች ይኖሯቸዋል፡፡

፫/ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እና የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ችሎቶች በአንድ ዳኛ ያስችላሉ፡፡

፬/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) እንደተጠበቀ ሆኖ፡-

ሀ) ከ፲፭ ዓመት በላይ የሚያስቀጡ የወንጀል ጉዳዮች በሶስት ዳኞች ይታያሉ፣

ለ) የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚያወጣው መመሪያ የተወሰኑ ጉዳዮች በፌደራል ከፍተኛ እና የፌደራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች በሶስት ዳኞች እንዲታይ ሊደረግ ይችላል፡፡

**፴. ስለ ፌደራል ፍርድ ቤቶች የማስቻያ ሥፍራ**

፩/ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የማስቻያ ሥፍራ አዲስ አበባ ይሆናል፡፡

፪/ የፌደራል ከፍተኛ እና የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤቶች የማስቻያ ስፍራ በአዲስ አበባ ከተማ፣ በድሬዳዋ ከተማ እና በፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ማደራጃ አዋጅ ቁጥር ፫፻፳፪/፲፭ በተመለከቱት እንዲሁም በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፸፰ ንዑስ አንቀጽ (፪) ወደፊት ሊወሰኑ በሚችሉ ቦታዎች ይሆናል፡፡

፫/ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) በተመለከቱት ቦታዎች የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤቶችን ያደራጃል።

**፴፩. የፌደራል ፍርድ ቤቶች የሥራ ቋንቋ**

፩/ የፌደራል ፍርድ ቤቶች የሥራ ቋንቋ አማርኛ ይሆናል፡፡

**29. Judges, Divisions and other Workers of the Federal High Court and Federal First Instance Court.**

1/ The Federal High Court and First Instance Court shall have judges and divisions required for their functions.

2/ The Federal High Court and First Instance Court shall have registrars, assistant judges, legal experts and other staff to be administered by their respective Presidents in accordance with Sub-Article (1)(b) of Article 19 and Sub-Article (2) of Article 23 of this Proclamation.

3/ The Division of the Federal High Court and Federal First Instance Court shall be presided by one judge.

4 without prejudice to the provisions of Sub-Article (3) of this Article:

a) criminal charges punishable with more than fifteen years' rigorous imprisonment shall be heard by a panel of three judges;

b) Certain cases may be heard by a panel of three judges in the Federal High Court and First Instance Court by a directive issued by the Federal Supreme Court.

**30. Place of Sittings of Federal Courts**

1/ The seat of the Federal Supreme Court shall be in Addis Ababa.

2/ The seats of Federal High Court and the First Instance Court shall be in Addis Ababa, Dire Dawa and in the places as stipulated in the Federal High Court Establishment Proclamation No. 322/2003 and in such other places as may be determined in accordance with Article 78 Sub-Article (2) of the Constitution.

3/ The Federal Supreme Court shall organize federal high court as provided in Sub-article (2) of this Article.

**31. Working Language of the Federal Courts**

1/ Amharic shall be the working language of the Federal Courts.

lawyer.et



፪/ የአማርኛ ቋንቋ ለማይችል ሰው ፍርድ ቤቱ ብቃት ያለው አስተርጓሚ ይመድብለታል፡፡

፫/ የምልክት ቋንቋ ለሚጠቀም አካል ጉዳተኛ በተመሣሣይ የምልክት ቋንቋ ችሎታ ያለዉ ባለሙያ ይመደብለታል፡፡

፬/ በየደረጃዉ ያሉ የፌደራል ፍርድ ቤቶች የተሟላ አገልግሎት መስጠት የሚያስችል የአስተርጓሚ ቢሮ ያደራጃሉ።

**፴፪. <u>በግልጽ ችሎት ስለማስቻል</u>**

፩/ የፌደራል ፍርድ ቤቶች ለሕዝብ ግልጽ በሆነ ሁኔታ ያስችላሉ፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተው ቢኖርም፦

ሀ) የተከራካሪዎቹን የግል ህይወት፤

ለ) የሀገሪቱን ደህንነት ለመጠበቅ፤

ሐ) የሕዝብ ሞራል ሁኔታ ወይም ግብረገብነት ለመጠበቅ፤

አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ፍርድ ቤቶች በዝግ ችሎት ያስችላሉ፡፡

**፴፫. <u>የዳኞች ከችሎት መነሳት</u>**

፩/ የፌደራል ፍርድ ቤት ዳኛ ከዚህ ቀጥሎ ከተመለከቱት ምክንያቶች በአንዱ ከችሎት ይነሳል፦

ሀ) ከተከራካሪዎቹ ከአንደኛው ወገን ወይም ከጠበቃዉ ጋር የሥጋ ወይም የጋብቻ ዝምድና ያለው እንደሆነ፤

ለ) ከተከራካሪዎቹ የአንደኛዉ ወገን ሞግዚት፣ ነገረ ፈጅ ወይም ጠበቃ በሆኑበት ጉዳይ ላይ የተነሳ ክርክር እንደሆነ፤

ሐ) ክርክር የተነሣበትን ጉዳይ አስቀድሞ በዳኝነት፣ በግልግል ዳኝነት፣ በዕርቅ ያየዉ ሆኖ ከተገኘ። ሆኖም አግባብ ባለዉ የሥነ-ሥርዓት ህግ መሰረት የይግባኝ ሰሚዉ ፍርድ ቤት በይግባኝ የቀረበለትን ጉዳይ ቀድሞ ወደወሰነዉ ፍርድ ቤት በመመለስ ሂደት ጉዳዩ የተመራለት ዳኛ ላይ ይህ ተፈጻሚ አይሆንም፤

2/ The Court shall provide a competent interpreter to a person who does not understand Amharic language.

3/ The Court shall similarly provide a sign language expert for concerned disabled person.

4/ Federal Courts at all levels shall organize Interpreters office with complete service.

**32. <u>Open Hearing</u>**

1/ Federal Courts shall conduct court proceeding in open court.

2/ Notwithstanding the provisions of Sub-Article (1) of this Article, cases may be heard in camera where it is found necessary to protect:

a) the right to privacy of the parties concerned;

b) National Security; and

c) public morality and public decency.

**33. <u>Withdrawal from proceedings or Removal of Judges</u>**

1/ A judge of a Federal Court shall be removed from his bench where:

a) he is related to one of the parties or the advocate thereof by consanguinity or by affinity:

b) the dispute relates to a case for whom he acts or acted as tutor, legal representative or advocate to one of the disputing parties;

c) he has previously acted as judge or mediator or an arbitrator in connection with the case or the subject matter of the dispute. This may, however, not applicable where a judge has previously acted as a judge of lower courts or appellate court in the process of remand;

lawyer.et



መ) ከተከራካሪዎቹ ወገኖች ከአንደኛዉ ወይም ከጠበቃዉ ጋር በፍርድ ቤት የተያዘ ክርክር ወይም ሙግት ያለዉ እንደሆነ፤

ሠ) ከዚህ በላይ ከንዑስ አንቀጽ (፩) (ሀ) እስከ (፩)(መ) ከተመለከቱት ምክንያቶች ውጭ ትክክለኛ ፍትሕ አይሰጥም የሚያሰኝ ሌላ በቂ ምክንያት ሲኖር፡፡

፪/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) መሠረት ዳኛው በችሎት ላይ ሊቀመጥ የማይገባዉ መሆኑን ሲያዉቅ ከችሎት ተነስቶ ሌላ ዳኛ መተካት አለበት፡፡

## ፴፬. ዳኛ ከችሎት እንዲነሳ ስለማመልከት

፩/ ከተከራካሪዎች አንደኛው በዚህ አዋጅ በአንቀጽ ፴፫ በተዘረዘሩት ምክንያቶች ዳኛ ከችሎት መነሳት ያለበት እንደሆነ ይህንኑ በሚመለከት ለፍርድ ቤቱ ማመልከቻ ማቅረብ ይችላል፡፡

፪/ ማመልከቻው የሚቀርበው ክርክሩ ከመጀመሩ በፊት ወይም ማመልከቻ ለማቅረብ ምክንያት መኖሩን አመልካቹ እንዳወቀ ወዲያውኑ መሆን አለበት፡፡

፫/ ዳኛው ብቻቸውን የሚያስችል ከሆነ እና ከችሎት ስለመነሳት የሚቀርበውን ማመልከቻ ተመልክቶ ጥያቄውን የተቀበለ እንደሆነ ከችሎት ይነሳል፡፡ ጥያቄውን ያልተቀበለ እንደሆነ ግን በዚያው ፍርድ ቤት በሚገኝ ሌላ ችሎት፤ ሌላ ችሎት ከሌለ የዚህኑ ፍርድ ቤት ውሣኔ ይግባኝ በሚያየው ፍርድ ቤት እንዲወሰን ይተላለፋል፡፡

፬/ ከችሎት እንዲነሳ ማመልከቻ የቀረበለት ዳኛ ከሌሎች ዳኞች ጋር የሚያስችል ከሆነ ማመልከቻው በዚያው ችሎት ባሉ ሌሎች ዳኞች ይወሰናል።

፭/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፫) መሠረት የሚቀርብ ጥያቄ ለአዲሱ ችሎት በደረሰ በ፲፭(አሥራ አምስት) ቀን ውስጥ መወሰን ያለበት ሲሆን የሚሰጠው ውሣኔ የመጨረሻና ይግባኝ የማይባልበት ይሆናል፡፡

፮/ የሚሰጠውን ውሣኔ ዳኛው ወዲያውኑ መፈጸም አለበት፡፡

## ፴፭. ማመልከቻው ስለሚያስከትለው ኪሣራ እና ቅጣት

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፬ መሠረት የሚቀርበውን ማመልከቻ ፍርድ ቤቱ ተገቢ አይደለም በማለት ሳይቀበለው ከቀረ የጉዳዩ ውጤት ከግምት ሳይገባ ኪሣራውን የሚከፍለዉ ማመልከቻውን ያቀረበዉ ሰው ይሆናል፡፡

d) he has a case pending in court with one of the parties or the advocate thereof;

e) There are sufficient reasons, other than those specified under Sub-Article (1)(a) to (1)(d) of this Article, to conclude that injustice may be done.

2/ The judge concerned shall withdraw as soon as he is aware that he should not sit, as provided in Sub-Article (1) of this Article, and shall be replaced by another judge.

## 34. Application for Removal of a Judge

1/ Where a party to a case find out that a judge should not sit for one of the reasons specified in Article 33 of this Proclamation, he shall submit a written application to the court requesting the removal of the judge.

2/ The application shall be made before the trial opens or soon after the party becomes aware of the reason for making such an application.

3/ Where a judge is sitting alone he shall, after considering the application, either withdraw or refer the matter for decision to another division of the same court. Where there is no other division the application shall be referred to the court in which appeal lies from the decision of the court.

4/ Where the judge is sitting with other judges, the matter shall be decided by the other judges who sit in the same division.

5/ A decision shall be rendered within 15(fifteen) days from the date such application reached the new division. and the decision shall be final with no appeal.

6/ A judge shall forthwith comply with a decision given under this Article.

## 35. Cost and Penalty of Application for Removal of a Judge

1/ Where the application submitted in accordance with Article 34 of this Proclamation is dismissed, the costs shall be borne by the applicant irrespective of the outcome of the case.

lawyer.et



፪/ ከተከራካሪዎቹ አንደኛዉ ወገን ዳኛው ከችሎት እንዲነሳ ያቀረበዉ ማመልከቻ በቂ ምክንያት የሌለዉ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ማመልከቻዉ ውድቅ በማድረግ በአመልካቹ ላይ ከብር ፩ሺህ እስከ ፫ሺህ (ከአንድ ሺህ ብር ያላነሰ ከሦስት ሺህ ብር) ያልበለጠ መቀጫ ሊጥል ይችላል፡፡ ሆኖም አቤቱታ አቅራቢዉ ሆን ብሎ የዳኛዉን ስም ለማጥፋት ወይም ክብር ለመጉዳት ወይም ጉዳዮችን ለማጓተት ዳኛው ከችሎት እንዲነሳ አቤቱታ ያቀረበ እንደሆነ ፍርድ ቤቱ ከብር ፫ሺህ እስከ ፯ሺህ (ከሦስት ሺህ ብር ያላነሰ ከሰባት ሺህ ብር) ያልበለጠ መቀጫ ሊጥል ይችላል፡፡

2/ Where a party makes an application without good cause, the court may, in addition to dismissing the application, impose a fine not less than 1000 Birr and not exceeding 3000 Birr. Provided however, where the applicant makes a malicious application with the intention of defaming or damaging his honor or delaying the proceedings, the court may impose a fine not less than 3000 Birr and not exceeding 7000 Birr.

## ምዕራፍ ሰባት

## ስለፌደራል ፍርድ ቤቶች በጀትና የሰው ሀብት አስተዳደር

## CHAPTER SEVEN

## BUDGET AND HUMAN RESOUCE MANAGEMENT OF FEDERAL COURTS

### ፴፮. የፌደራል ፍ/ቤቶች የበጀት አስተዳደር ነፃነት

፩/ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፌደራሉን መንግስት የዳኝነት አካል የሚያስተዳድርበትን በጀት ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርቦ ያስወስናል፤ሲፈቀድም በጀቱን ያስተዳድራል፡፡

፪/ ገንዘብ ሚኒስቴር ምክር ቤቱ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤቱ ያፀደቀለትን ዓመታዊ በጀት ፍርድ ቤቱ የፋይናንስ አሰራርን ተከትሎ በሚያቀርበው ጥያቄ መሠረት በየሩብ ዓመቱ መጀመሪያ የሚያስፈልጋቸውን በጀት በቅድሚያ ወደ ፌደራሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የባንክ ሂሳብ ማስገባት አለበት፡፡

### 36. Budgetary Adminstration Autonomy of Federal Courts

1/ Federal Supreme Court shall submit the budget of federal courts to the House of Peoples' Representatives, and administer in the approval of the same.

2/ Ministry of Finance shall credit annual budget of Federal Courts to federal supreme court account on the 1st of each quarter year with request of the court following financial procedure.

### ፴፯. ስለ ፌደራል ፍርድ ቤቶች በጀት

፩/ በሕገመንግሥቱ አንቀጽ ፸፱ (፮) በተደነገገው መሰረት የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት የፌደራል ፍ/ቤቶችን በጀት አዘጋጅቶ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ያቀርባል፡፡

፪/ የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት ፕሬዚዳንት ከሌሎች የፍርድ ቤት ኃላፊዎች ጋር በመሆን ሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በመቅረብ የበጀት ጥያቄውን ያስረዳል፡፡

፫/ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ለፌደራል ፍርድ ቤቶች የጸደቀላቸውን በጀት አጠቃቀም አስመልክቶ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሪፖርት ያቀርባል፡፡

፬/ የፌደራል ፍ/ቤቶች የበጀት ዓመት የፌደራል መንግሥቱ የበጀት ዓመት ይሆናል፡፡

### 37. Budget Of Federal Courts

1/ In accordance with Art 79 (6) of the Constitution, the president of the Federal Supreme Court shall prepare budget for Federal Courts and submit the same to the House of People`s Representatives.

2/ The President shall, together with other judicial officials, shall explain the budget request of the Federal Courts before the House of Peoples' Representatives.

3/ The Federal Supreme Court shall present report to the House of Peoples' Representatives regarding the administration of budget to Federal Courts.

4/ The fiscal year of the Federal Courts shall be the same as the fiscal year of the Federal Government.

lawyer.et



## ፴፰. የፌደራል ፍርድ ቤቶች የስራ ጊዜ

፩/ የፌደራል ፍርድ ቤቶች እና ዳኞች የስራ ሰዓት ከሌሎች የመንግስት መስሪያ ቤቶች የስራ ሰዓት ጋር ተመሳሳይ ይሆናል።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተመለከተዉ ቢኖርም የፌደራል ፍርድ ቤቶች በየአመቱ ከነሐሴ ፩ እስከ መስከረም ፴ ድረስ ዝግ ይሆናሉ።

፫/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተመለከተዉ ቢኖርም በትርፍ ጊዜ በሚሰሩ ዳኞች ፍርድ ቤቶቹ ከስራ ጊዜ ዉጭ አስቸኳይ ጉዳዮችን እንዲያስተናግዱ ሊደረግ ይችላል። ዝርዝሩ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚያወጣዉ መመሪያ ይወሰናል።

## ፴፱. የሰው ሀብት

፩/ የፌደራል ፍርድ ቤቶች ከዳኞች ውጭ ያሉ የራሳቸውን ሠራተኞች የፌደራል የመንግስት ሠራተኞች አዋጅ መሠረታዊ መርሆዎችን በመከተል የመመልመል፣ የመቅጠርና የማስተዳደር ነፃነት አላቸው ፡፡

፪/ የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (፩) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ከዳኞች ዉጭ ያሉ ሰራተኞች ምልመላ፣ ቅጥር፣ ምደባ፣ ዕድገት፣ ዝውውር፣ሥልጠና፣ የደመወዝ ጭማሪ፣ የጥቅማ ጥቅም ክፍያ፣ የሰራተኞች የዲሲፕሊን እና ተያያዥ ጉዳዮች የሚወሰነው ይህንን አዋጅ ለማስፈፀም በሚወጣው ደንብ አማካኝነት ይሆናል፡፡

፫/ የአስተዳደር ሠራተኞች መብትና ጥቅማ ጥቅም በመንግስት ሠራተኞች አዋጅ ለሌሎች የመንግስት ሠራተኞች ከተፈቀደው ያነሰ ሊሆን አይችልም፡፡

## ፵. ኦዲት

የፌደራል ፍርድ ቤቶች የሂሳብ መዝገብና የበጀት አጠቃቀም በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፴፫ መሰረት መከናወኑን በፌደራል ዋና ኦዲተር በየአመቱ ይመረመራል፡፡

## ምዕራፍ ስምንት
## ስለፌደራል ፍርድ ቤቶች ጉባዔ

## ፵፩. የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ጉባዔ

የፌደራል ፍርድ ቤቶች አንድ የፌደራል ፍርድ ቤቶች ጉባዔ (ከዚህ በኋላ "ጉባዔ" እየተባለ የሚጠራ) ይኖራቸዋል፡፡

## 38. Callander Of Federal Courts

1/ The work hours of the federal courts and federal judges shall be the same with the working hours of other government institutions and civil servants.

2/ Notwithstanding Sub-Article (1) of the provision of this Article, Federal Courts shall be closed from July 8 to September 12 every year.

3/ Notwithstanding Sub-Article (1) and (2) of this Article, emergency cases shall be tried in courts by judges who work in over-time voluntarily. Particulars shall be determined in directives to be issued by supreme court.

## 39. Human Resources

1/ Federal Courts shall have independence to recruit, hire and administer their own non-judicial personnel pursuant to fundamental principles of Federal Civil Servant Proclamation.

2/ without prejudice to Sub-Article (1) provision of this Article the recruitment, hire, placement, promotion, transfer, training, salary increments, benefits, disciplinary matters and other related matters of non-judicial personnel shall be governed by a regulation to be issued for the implementation of this Proclamation.

3/ The rights and benefits of non-judicial personnel cannot be less than the rights of other government employees provided for by the civil service law.

## 40. Audit

The books of accounts and utilization of budget of Federal Courts shall be audited annually by the Federal Auditor General.

## CHAPTER EIGHT
## THE PLENUM OF THE FEDERAL COURTS

## 41. Plenum of the Federal Courts

The Federal Courts shall have a Federal Courts Plenum (hereinafter referred to as" the Plenum.")

lawyer.et



**፵፪. <u>የጉባዔው አባላት</u>**

፩/ የጉባዔው አባላት የፌደራል ፍርድ ቤቶች ኘሬዚዳንቶች፣ ምክትል ኘሬዚዳንቶች፣ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዳኞች፣ በፌደራል ከፍተኛ እና በመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት ዳኞች የተወከሉ ሁለት ዳኞች ከእያንዳንዳቸዉ አንድ ወንድ አንድ ሴት፤ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ኘሬዚዳንቶች፣ የአዲስ አበባ እና የድሬድዋ ከተማ ፍርድ ቤቶች ኘሬዚዳንቶች ይሆናሉ፡፡

፪/ በጉባዔው ላይ ፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ድምፅ የመስጠት መብት ሳይኖረዉ ይሳተፋል፡፡

፫/ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ያልተጠቀሱ ዳኞች፤ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አባላት እና አግባብ ያላቸው የመንግሥት መሥሪያ ቤቶችን፣ ማኀበራትን ፣ ድርጅቶችን ፣ ከፍተኛ የሕግ ትምህርት ተቋማት እና የሳይንስ ተቋሞችን የሚወክሉ ሰዎች ወይም ሌሎች ግለሰቦች በጉባዔው እንዲሳተፉ በፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሊጋበዙ ይችላሉ፡፡ ሆኖም ድምፅ የመስጠት መብት አይኖራቸውም፡፡

**፵፫. <u>የጉባዔው ሥልጣንና ተግባር</u>**

ጉባዔው ከዚህ የሚከተሉት ሥልጣንና ተግባራት ይኖሩታል፦

፩/ በዳኝነት ነጻነት፣ ገለልተኝነት፣ ተጠያቂነት እና በፍትህ አስተዳደር ረገድ በኢትዮጵያ በየትኛዉም ቦታ ባጋጠሙ ችግሮች ላይ ተወያይቶ መፍትሔ መስጠት፣

፪/ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት እና ለዳኞች አስተዳደር ጉባኤ በዚህ አዋጅ እና በሌሎች አግባብነት ባላቸዉ ህጎች የተሰጠዉ መመሪያ የማዉጣት ስልጣን እንደተጠበቀ ሆኖ የፌደራል ፍርድ ቤቶች የዳኝነት አሠራርን ለማሻሻል የሚረዱ መመሪያዎችና ውሳኔዎችን ማሳለፍ፣

፫/ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ አዳዲስ ሕጎች እንዲወጡ ወይም ነባር ሕጎች እንዲሻሻሉ ለሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሃሣብ ማቅረብ፣

፬/ የዳኝነት ሥራ አካሄድን ለማቀላጠፍና ለማጠናከር የሚረዱ ሌሎች ተግባራትን ማከናወን፤ እና

፭/ ለጉባዔው ሥራ አፈፃፀም አስፈላጊውን መመሪያ ማውጣት፡፡

**42. <u>Members of the Plenum</u>**

1/ Members of the plenum shall be the Presidents, Vice-Presidents of the Federal Courts, Judges of the Federal Supreme Court, two judges, one woman and one man, from each Federal High Court and Federal First Instance Court, Presidents of Regional Supreme Courts, Presidents of Addis Ababa and Dire Dawa City Courts.

2/ The Federal Attorney General shall participate in the sessions of the Plenum without, having the right to vote.

3/ Judges not referred to under Sub-Article (1) of this Article, members of the House of Peoples' Representatives and representatives of appropriate government offices, associations, organizations, higher legal education institutions or scientific institutions or other individuals may be invited by the Federal Supreme Court to participate in the Plenum without, however, having the right to vote.

**43. <u>Powers and Duties of the Plenum</u>**

The Plenum shall have the following powers and duties:

1/ deliberate on problems encountered within Ethiopia with respect to independence of the judiciary, accountability and administration of justice and work out remedies thereto;

2/ without prejudice to the power given to Federal Supreme Court and the Federal Judicial Administration Council to issue directive in accordance with this Proclamation and other relevant laws, issue directives and pass decisions that help improve the judicial practices of Federal Courts;

3/ submit proposals to the House of Peoples Representatives for the enactment of new laws or the amendment of existing ones as if necessary;

4/ perform such other functions that help to make the judiciary efficient and strong; and

5/ issue directives necessary for the proper carrying out of its duties.

lawyer.et



## ፵፬. የጉባዔው አሠራር ሥነ-ሥርዓት

፩/ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ኘሬዚዳንት የጉባዔው ሰብሳቢ ይሆናል፡፡

፪/ ጉባዔው የራሱን ፀሐፊ ይመድባል፡፡

፫/ ጉባዔዉ ስራዉን ለማከናወን የሚረዱ ኮሚቴዎችን ያዋቅራል፡፡

፬/ ጉባዔዉ የራሱ ላይዘን ቢሮ እና ተጠሪዎች አስፈላጊ በሆኑ ፍርድ ቤቶችያቋቁ‌ማል፡፡

፭/ ጉባዔው የሥራ ባልሆኑ ቀናት በዓመት አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፡፡ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ተጨማሪ ስብሰባም መጥራት ይችላል፡፡

፮/ ከጉባዔው አባላት ሁለት ሶስተኛው ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡፡ ውሣኔ በድምፅ ብልጫ ይተላለፋል፡፡ ድምፅ እኩል ለእኩል በተከፈለ ጊዜ የጉባዔው ሰብሳቢ ወሳኝ ድምፅ ይኖራቸዋል።

## ምዕራፍ ዘጠኝ

## የፍርድ ቤት መር አስማሚነት እና የጉዳዮች አስተዳደር

## ፵፭.የፍርድ ቤት መር አስማሚነት

፩/ በፌደራል የመጀመሪያ ፍርድ ቤት እና ከፍተኛ ፍርድ ቤት ከሚቀርቡ ጉዳዮች ዉስጥ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚያወጣዉ መመሪያ የሚወሰኑ በዋናነት የፍትሀብሄር ጉዳዮች በፍርድ ቤቶች በሚቋቋም የፍርድ ቤት መር አስማሚነት በኩል እንዲያልፉ ይደረጋል።

፪/ ተከራካሪ ወገኖች በፍርድ ቤት መር አስማሚነት በኩል ጉዳያቸዉን በስምምነት ካልጨረሱ ይህንኑ የሚገልጽ በአስማሚዎቹ የተፈረመ ደብዳቤ ለፍርድ ቤት በማቅረብ የፍርድ ሂደቱ እንዲቀጥል ይደረጋል።

፫/ የተስማሙ ከሆነ የስምምነቱ ሁኔታዎች በአስማሚዉ በግልጽ ተለይተዉ ከቀረቡ እና ተከራካሪዎቹ ከፈረሙበት በኋላ አስማሚዉ ይህን ሰነድ ለፍርድ ቤት ቀርቦ እንዲጸድቅ ያደርጋል። ሰነዱ የቀረበለት ፍርድ ቤትም ሰምምነቱ ለህግ እና ለሞራል ተቃራኒ አለመሆኑ ከተረጋገጠ በኋላ እንዲጸድቅ ያደርጋል።

፬/ የጸደቀዉ የስምምነት ሰነድ እንደማንኛዉም የፍርድ ቤት ዉሳኔ ተፈጻሚ ይሆናል።

## 44. Working Procedure of the Plenum

1/ The President of the Federal Supreme Court shall be the chairperson of the Plenum.

2/ The plenum shall designate its secretary.

3/ The Plenum shall designate committees to assist its functions.

4/ The Plenum shall, where necessary, have its own liaison office and focal persons in courts.

5/ The Plenum shall convene once a year on non-working days. additional meetings may be called when necessary.

6/ Two- thirds of the members of the Plenum shall constitute a quorum. Decisions shall be adopted by a majority vote. In case of a tie the chairperson shall have a casting vote.

## CHAPTER NINE

## COURT ANNEXED MEDIATION AND CASE MANAGEMENT

## 45. Court Annexed Mediation

1/ Among the cases that are to be heard by the Federal First Instance court and Federal High Court, mainly civil cases shall be referred to Court Annexed Mediation in accordance with directive issued by the Supreme Court.

**2/** Where the parties have failed to resolve their dispute through Court Annexed mediation, the court proceedings shall be initiated by filing a letter signed by the mediators to that effect.

**3/** Where the parties have reached an agreement, the mediator shall cause the approval of the settlement agreement by a court by clearly stating the terms of settlement and having it signed by the parties.

**4/** The approved settlement agreement shall be executed like any decision of a court.

lawyer.et



፭/ በአንደኛዉ ተከራካሪ ወገን ያለመቅረብ ምክንያት የመስማማት ሂደቱ ካልተሳካ አስማሚዉ ይህንኑ በመግለጽ ለፍርድ ቤቱ ሪፖርት ያደርጋል። በድርድሩ ያልተገኘ ወገን ተገቢውን ክፍያ ከፍሎ መደበኛው የፍርድ ሂደትም ይቀጥላል።

፮/ በፍርድ ቤት መር አስማሚነትም ይሁን በሌላ አማራጭ የግጭት መፍቻ ዘዴ ግራ ቀኙ ከተስማሙ በደንቡ መሰረት ወጭዎች ተቀንሰዉ የከፈሉት የዳኝነት ክፍያ ተመላሽ ይደረግላቸዋል።

፯/ የፍርድ ቤት መር አስማሚነት ተግባራትን የሚያግዝ እና አስማሚዎችን የሚቆጣጠር የፍርድ ቤት አመራሮችን፣ ዳኞችን እና የአስማሚነት ከፍተኛ ባለሙያዎችን ያካተተ ኮሚቴ የጠቅላይ ፍርድ ቤት ሊያቋቁም ይችላል፡፡

፰/ የዚህን ድንጋጌ ለማስፈጸም የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ዝርዝር መመሪያ ያወጣል።

## ፵፮. ስለ አስማሚነት መርሆዎች

፩/ በፍርድ ቤት መር አስማሚነት የሚደረገዉ ማንኛዉም ሂደት በእኩልነት እና በባለጉዳዮቹ ሙሉ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ መሆን አለበት።

፪/ በማስማማት ሂደቱ ተከራካሪ ወገኖች የሚሰጡት የእምነት ቃሎች ወይም ማንኛዉም ንግግሮች ለፍርድ ቤት በማስረጃነት አይቀርቡም። ለዚህም አስማሚዉ ማረጋገጫ ይሰጣል።

፫/ በፍርድ ቤት አስማሚነት በኩል የሚደረጉ ማናቸዉም የሃሳብ ልዉዉጦች ሚስጥራዊነት የተጠበቀ ነዉ።

## ፵፯. ስለ አስማሚዎች

፩/ የአስማሚነት ስልጠና ወስደዉ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የሚያወጣዉን ምዘና ያለፉ ቢያንስ በህግ የመጀመሪያ ዲግሪ ያላቸዉ እና ከአምስት አመት ያላነሰ ጊዜ በህግ ሙያ ያገለገሉ አስማሚ ሆነዉ ሊመረጡ ይችላሉ።

፪/ የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተገለጸዉን ያሟሉ ባለሙያዎች የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚያዘጋጀዉ የአስማሚዎች ሮስተር መዝገብ ዉስጥ እንዲካተቱ ይደረጋሉ።

፫/ ፍርድ ቤቱ እንደአስፈላጊነቱ በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት ብቁ አስማሚዎችን ሊቀጥር ይችላል።

**5/** Where the proceeding is interrupted due to absence of the other party, the mediator shall report to the court by specifying the reason for the interruption and the court proceedings shall be initiated after the absency party paid appropriate fee.

**6/** Where the parties have reached an agreement through court annexed mediation or other dispute resolving mechanism, any paid court fee shall be reimbursed after deducting mediation expenses according to the Regulation.

7/ Supreme Court shall establish a Committee from Court Leaders, Judges and Seiner Mediators which may support court annexed mediation activity and supervise mediators.

**8/** The Federal Supreme Court shall issue directive for the implementation of this Article,

## 46. Principles of Mediation

1/ The parties shall be free and equal in any process of court annexed mediation.

2/ Communications of the parties shall not be admissible as evidence in the process of litigation. And the mediator shall give assurance for same.

3/ All communication of the court-annexed mediation shall be confidential.

## 47. Mediators

1/ A person with a bachelor degree in law and with at least five years of experience in the field of law and who has taken training in mediation and has fulfilled the criteria set by the Supreme Court may be appointed as Mediator.

2/ A professional who has fulfilled the requirements provided for in Sub-Article (1) of this Article shall be entered in the roster of mediators prepared by the Federal Supreme Court.

3/ The court may hire mediators as permanent or temporary employee as may be necessary.

lawyer.et



፬/ በዚህ አንቀፅ ከንዑስ አንቀፅ (፩) እስከ (፫) የተጠቀሰው ቢኖርም ከህግ ሙያ ውጭ በሆነ ሌላ ሙያ ከፍተኛ ልምድ ያላቸው ኤክስፐርቶች ከሙያቸው ጋር ተያያዥ የሆኑትን ሊጨምር ይችላል፡፡

**፵፰. <u>ስለ ክፍያ</u>**

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፵፮ ንዑስ አንቀጽ (፩) እና (፪) የተገለጹ አስማሚዎች የጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚያወጣዉ መመሪያ የሚወሰን ለአስተዳደራዊ ጉዳይ እና ዓመታዊ ክፍያ ይከፍላሉ።

፪/ አስማሚዎች በባለጉዳዮች ተመርጠዉ የማስማማት አገልግሎት ከሰጡ ተገቢዉ ክፍያ ይከፈላቸዋል።

፫/ በማስማማቱ ሂደት ዉስጥ የሚያልፉ ባለጉዳዮች ለፍርድ ቤት መር አስማሚነት ተገቢዉን ክፍያ ይፈጽማሉ።

፬/ ክፍያን በሚመለከት ዝርዝር መመሪያ በጠቅላይ ፍርድ ቤት ይወጣል።

**፵፱. <u>የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር</u>**

፩/ የፌደራል ፍርድ ቤቶች የሚቀርቡላቸዉን ጉዳዮች የሚስተናገዱበት ወይም የሚጠናቀቁበትን የጊዜ ሰሌዳ ገደብ በማስቀመጥ የፍትህ አሰጣጥ ስርዓቱ የተሳለጠ እና ጥራቱ የሚረጋገጥበት የጉዳዮች ፍሰት አስተዳደር ተግባራዊ ያደርጋሉ።

፪/ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተገለጸዉን ለማስፈጸም ዝርዝር መመሪያ ያወጣል።

**፶. <u>በቴክኖሎጅ የተደገፈ የመዝገብ አመራር ሥርዓት ስለመዘርጋት</u>**

፩/ የፌደራል ፍርድ ቤቶች በማንኛዉም የፍርድ ቤት ደረጃ የሚቀርቡ የፍትሀብሄር ወይም የወንጀል ጉዳይ ክርክሮችን አዳዲስ የመረጃ ቴክኖሎጅዎችን በመጠቀም ዳጂታል ወይም አዉቶሜትድ በሆነ መንገድ እንዲከናወኑ ሥርዓት ሊዘረጉ ይችላሉ።

፪/ ተከራካሪ ወገኖች በተዘረጋዉ ሥርዓት መሰረት ክርክሮቻቸዉን የማካሄድ ግዴታ አለባቸዉ።

፫/ ዝርዝሩ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚያወጣዉ መመሪያ ይወሰናል።

## <u>ምዕራፍ አስር</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

4/ Notwithstanding Sub-Article (1) up to (3) of this Article, experienced non-legal professionals shall be included in areas related to their profession.

**48. <u>Fees</u>**

1/ The Mediators mentioned in Sub-Article (1) and (2) of Article 46 shall pay annual and administration fee as determined by the Federal Supreme court directive.

2/ Mediators who are elected by the parties and provides mediation service shall be entitled to appropriate fee for their service.

3/ Parties to a court annexed mediation shall pay appropriate fee for the service.

4/ The Federal Supreme Court shall issue detail directive regarding fees.

**49. <u>Case-Flow Management</u>**

1/ Federal Courts shall implement case flow management system in order to make the system of rendering of justice efficient and ensure its quality by setting a time frame filing and disposition of cases.

2/ The Federal Supreme Court shall issue detail directive for the implementation of the provision of Sub-Article (1) of this Article.

**50. <u>Technology Based File Management System</u>**

1/ The Federal Courts may introduce a system for digitalizing or automating the filing and management of civil or criminal cases at any level of courts by using new information technology (IT).

2/ Parties to a dispute shall have the obligation to conduct their litigation by using the system.

3/ The detail shall be determined by a directive to be issued by the Federal Supreme Court.

## <u>CHAPTER TEN</u>

## <u>MISCELLANEOUS PROVISIONS</u>

lawyer.et



## ፶፩. የፍርድ ቤት ውሣኔዎችና ትዕዛዞች

፩/ በማንኛውም የፌደራል ፍርድ ቤት የተሰጠ ውሳኔ እና ትዕዛዝ በህግ እስካልተለወጠ ድረስ የፀና ሆኖ ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

፪/ የፌደራል ፍርድ ቤቶች የሚሰጧቸዉን ዉሳኔዎች ወይም ትዕዛዞች በሁሉም የኢትዮጵያ ክልሎች ዉስጥ ተፈጻሚ ይሆናሉ፡፡ በማንኛዉም ክልል ዉስጥ የሚገኝ የመንግስት አካል፣ተቋም ወይም መንግስታዊ ያልሆነ ድርጅት ወይም ማንኛዉም ሰው ውሳኔዎቹን ወይም ትዕዛዞቹን የመፈጸም እና የማስፈጸም ግዴታ አለበት።

፫/ ማንኛዉም ሰዉ በዚህ አዋጅ የተጣለበትን ግዴታ የማይወጣ ከሆነ በዚህ አዋጅና አግባብ ባለው ሌላ ህግ ተጠያቂ ይሆናል።

፬/ አንድን ጉዳይ ሁለት ወይም ከዚያ በላይ የክልል ወይም የፌደራል ፍርድ ቤቶች ወይም የአዲስ አበባ ወይም የድሬዳዋ ከተሞች ሥልጣናችን ነው ብለው የያዙት ወይም ሥልጣናችን አይደለም ብለው የመለሱት እንደሆነ ስልጣኑን በሚመለከት የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ተገቢውን ትዕዛዝ ይሰጥበታል፡፡

## ፶፪. የወንጀል ተጠያቂነት

፩/ የፍርድ ቤት ወይም የዳኞችን በነጻነት መስራት የሚጋፋ ወይም በዳኞች ላይ ተጽእኖ የሚያደርግ ወይም ለማድረግ የሞከረ ማንኛው ሰዉ በሌላ ህግ ከፍ ያለ ቅጣት ከሌለ በቀር ከሦስት ወር እሥራት ባላነሰ ከሁለት ዓመት ባልበለጠ ጽኑ እስራት ይቀጣል።

፪/ የፍርድ ቤትን ትዕዛዝ ወይም ዉሳኔ የማይፈጽም ወይም ለመፈፀም መሰናክል የሚፈጥር ወይም ሲጠየቅ ለመፈፀም ተባባሪ የማይሆን ማንኛዉም ሰዉ በሌላ ህግ ከፍ ያለ ቅጣት ከሌለ በቀር ከሁለት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት ወይም ከአምስት ሺህ ብር በማይበልጥ ገንዘብ ይቀጣል።

## ፶፫. የዉጭ አማካሪ ምክር ቤት ስለማደራጀት

፩/ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከቀድሞ የፌደራል ፍርድ ቤት ዳኞች፣ ከፍተኛ ልምድ እና ብቃት ካላቸዉ የህግ ባለሙያወች፣ ከዩኒቨርስቲ ምሁራን የተዉጣጡ ያለክፍያ የሚሰሩ የዉጭ አማካሪዎችን በመምረጥ የዳኝነት ሥርዓት የዉጭ አማካሪ ምክር ቤት ሊያደራጅ ይችላል።

## 51. Decisions and Orders of the Federal Courts

1/ Unless otherwise provided by law, decision and order rendered by any Federal Court shall be binding.

2/ Decisions or orders of the Federal Courts shall be executed within Ethiopia. Any government body or institution, non-government organization or person residing in any region shall have the obligation to execute or cause to be executed such decisions or orders.

3/ Any person who fails to discharge his obligation imposed by this Proclamation be shall held accountable in accordance with this Proclamation and any other relevant law.

4/ Where two or more Regional or Federal Courts or Addis Ababa or Dire Dawa cities Courts claim or disclaim jurisdiction over a case, the Federal Supreme Court shall give the appropriate order thereon.

## 52. Criminal Liability

1/ Whosoever obstructs the independence of court and judges or put pressure or attempts to put pressure on judges is punishable, unless a more severe penalty is provided for in an-other law, with simple imprisonment not less than three months and with rigorous imprisonment not exceeding two years.

2/ Whosoever fails to obey a court order or decision hinders the execution thereof or fails to cooperate or give assistance when so requested is punishable, unless the more severe penalty is provided for in another law, with simple imprisonment not exceeding two years or with fine not exceeding birr 5, 000.

## 53. External Judicial Advisory Council.

1/ The Federal Supreme Court may establish an external advisory council composed of ex-judges of the federal courts, highly experienced and qualified legal professionals, university Professors who serves in the council for free.

lawyer.et



፪/ የአማካሪ ምክር ቤቱ የፍርድ ቤቱን የዳኝነት ሥርዓት ለማሻሻል የሚረዱ አስገዳጅ ያልሆኑ ምክረ ሃሳቦችን በማመንጨት እንዲሁም ሌሎች በፍርድ ቤቱ የሚሰጡትን ስራዎች በማከናወን የፍርድ ቤቱን አስተዳደር ያግዛል።

፫/ አማካሪ ምክር ቤቱ ስራዉን በሚያከናዉንበት ጊዜ የዳኝነት ነጻነትን እና የዳኝነት ሥነ-ምግባርን በማይጻረር መልኩ በጥብቅ ዲስፕሊን እና በከፍተኛ ሀላፊነት ስራቸዉን ማከናዎን ይጠበቅባቸዋል።

፬/ ዝርዝሩ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በሚያወጣዉ መመሪያ ይወሰናል።

**፶፬. ስለ ይግባኝ**

ማንኛውም በሥር ፍርድ ቤት ውሳኔ ቅር የተሰኘ ሰው አግባብ ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ ሊጠይቅ ይችላል፡፡

**፶፭. ደንብ እና መመሪያ የማውጣት ሥልጣን፡፡**

፩/ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡

፪/ የፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይህንን አዋጅ ወይም አዋጁን ተከትሎ የሚወጣውን ደንብ ለማሰፈፀም የሚያስችል መመሪያ ያወጣል፡፡

**፶፮. የመሸጋገሪያ ድንጋጌዎች**

፩/ ይህ አዋጅ ተፈጻሚ ከመሆኑ በፊት የተጀመሩ ጉዳዮች በተጀመሩበት ፍርድ ቤት እና በነባሩ ህግ መስተናገዳቸዉ ይቀጥላል።

፪/ በዚህ አዋጅ ከአንቀጽ ፲፩ እስከ አንቀጽ ፲፭ ድረስ የተጠቀሱት ድንጋጌዎች ተፈፃሚ የሚሆኑት አዋጁ ከፀደቀ ከ፮ ወር በኋላ ይሆናል።

፫/ የአስተዳደር ሠራተኞች መተዳደሪያ ደንብ እስከሚወጣ ድረስ የሠራተኞች ቅጥር፣ ምደባ፣ ዝውውር፣ እድገትና አስተዳደር የዚህን አዋጅ መርሆዎች ሳይቃረን ቀድሞ ሲሰራበት በነበረው ሕግ መሰረት ይቀጥላል፡፡

**፶፯. የተሻሩ እና ተፈጻሚነት የማይኖራቸው ሕጎች**

፩/ በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፶፮ ላይ የተጠቀሰው እንደተጠበቀ ሆኖ ፣ የፌደራል ፍርድ ቤቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፰ እና አዋጁን ለማሻሻል የወጡ ቁጥራቸው ፩፻፴፰/፲፱፻፺፩፣ ፪፻፶፬/፲፱፻፺፫ ፣ ፫፻፳፩/፲፱፻፺፭ እና ፬፻፶፬/፲፱፻፺፯ የሆኑ አዋጆች በዚህ አዋጅ ተሽረዋል፡፡

2/ The Advisory Council shall support administration of the court by providing non-binding recommendations and perform such other functions assigned to it by the court.

3/ The Advisory Council shall perform its functions by complying with the principle of judicial independence and undertake its function with strict discipline.

4/ The details shall be provided by directive issued by the Federal Supreme Court.

**54. Leave of Appeal**

Any person who wishes to appeal from the decision of lower court shall have a right to appeal to appropriate court

**55. Power to Issue Regulation and Directives**

1/ The House of Peoples' Representatives may issue Regulation for the implementation of this Proclamation.

2/ The Federal Supreme Court may issue directives for the implementation of this Proclamation and Regulation issued under this Proclamation.

**56. Transitory Provisions**

1/ All pending cases shall continue to be heard by the same court in accordance with the repealed/former/ law.

2/ The provisions of Article 11 to Article 15 of this Proclamation shall come into force after six months as of the effective date of this Proclamation.

3/ Recruitment, placement, promotion and transfer of non-judicial personnel shall continue to be governed by the repealed law in so far as they are consistent with this Proclamation until a regulation is issued to that effect.

**57. Repealed and Inapplicable Laws**

1/ Without prejudice to the provision of Article 56 of this proclamation Federal Courts Proclamation No. 25/1996 as amended by Proclamations Nos. 138/1998, 254/2001, 321/2003 and 454/2005 are here by repealed.

lawyer.et



፪/ ይህን አዋጅ የሚቃረን ወይም በዚህ አዋጅ የተሸፈኑ ጉዳዮችን የሚመለከት ማናቸውም ሕግ ተፈጻሚነት አይኖረውም፡፡

**፶፰. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

የዚህ አዋጅ አንቀፅ ፶፮ ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ይህ አዋጅ በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ከፀደቀበት ከጥር ፲፫ ቀን ፪ሺ፲፫ ዓ.ም ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ ሚያዚያ ፲፰ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት**

2/ Any law inconsistent or dealings related to matters provided under this Proclamation shall not be applicable.

**58. <u>Effective Date</u>**

Without prejudice to Article 56 provision of this Proclamation, shall come in to force as of the date ratified by the House on 21st day of January, 2021.

**Done at Addis Ababa, on this 26th day of April, 2021.**

**SAHILEWORK ZEWEDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**